| | |
|---|---|
| **ዩኒቨርሲቲ** | **ዲላ ዩኒቨርሲቲ** |
| **ኮሌጅ** | የማህበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ |
| **ትምህርት ክፍሉ** | የአማርኛ ቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ |
| **የሞጁሉ ርዕስ** | ስነጽሁፋዊ ሂስ እና የፈጠራ ድርሰት (Literary criticism and Creative writing)ELAm-M3121 |
| **የኮርሱECTS(Cr.Hr)** | 5 ECTS (3 Cr. Hr.) |
| **የኮርሱ ስምና መለያ ቁጥር** | የፈጠራ ድርሰት (Creative Writing) (ELAm3124) |
| **የኮርሱ መረጃ** | **የትምህርት ዘመን-** 2012 ዓ.ም. **መንፈቀ ዓመት-** ሁለት<br>**የማስተማሪያ ቀናት-** ሐሙስ |
| **የኮርሱ መምህር** | ምስራቅ ጠና |
| **መምህሩ የሚገኝበት መረጃ** | የቢሮ ስልክ----------046 331 30 58<br>ኢሜል----------- Misrak719@gmail.com<br>የማማከሪያ ሰዓት ---- **ማክሰኞ** 7:30-9:30<br>**አርብ** 07:30-09:30 |
| **ለኮርሱ የተሰጠው ጊዜ** | 5cp/135ሰዓት |

| **የመምህሩና የተማሪዎች የስራ ድርሻ (በሰዓት)** | **ገለጻ** | **ማጠናከሪያ** | **የቡድን ስራ** | **የግል ስራ** | **የቤተ-መጻህፍት ስራ** | **የቤት ጥናት** | **ምዘና እና ምጋቤ ምላሽ** | **ጠቅላላ ሰዓት** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 48 | 4 | 12 | 11 | 24 | 24 | 12 | 135 |

| | |
|---|---|
| **የኮርሱ ገለጻ** | ይህ ኮርስ የፈጠራ ድርሰት ምንነት እና አገልግሎት ቅኝት፣የፈጠራ ድርሰት ተግዳሮቶችና መፍትሄዎች፣ የፈጠራ ድርሰት መሰረታዊያን ወይም የፈጠራ ድርሰትን ለመጻፍ ሊተገበሩ የሚገቡ ጉዳዮች ውይይት እና የተግባር ፍተሻ፣የፈጠራ ድርሰት አይነቶች እና ስልቶቻቸው በተመለከተ ጽንሰ ሃሳበባዊ ጥናት እና ተግባራዊ ሙከራዎችን ያካተተ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ቀድመው በሥነ-ጽሑፍ መሠረታውያን እንዲሁም በመሰረታዊ የጽህፈትኮርስ የተማሩትን፣ ከዚህ ኮርስ ከሚያገኙት እውቀት ጋር እያናበቡና እያገናዘቡ ትምህርቱን እንዲከታተሉ ይመከራሉ፡፡ |
| **የኮርሱ አጠቃላይ አላማ** | <u>የኮርሱ አላማ</u>፡- ከዚህ ኮርስ ፍፃሜ በኂላ ተማሪዎች፡-<br>✓ የፈጠራ ድርሰት ምንነትን ይገልጻሉ፡፡<br>✓ የፈጠራ ድርሰት ዐይነቶችን እና ስልቶቻቸውን ይዘረዝራሉ፡፡<br>✓ የፈጠራ ድርሰት አጻጻፍ ሂደቶችን ተከትለው ይጽፋሉ፡፡<br>✓ ልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰቶችን ይጽፋሉ፡፡<br>✓ ኢ-ልቦለድ የፈጠራ ድርሰቶችን ይጽፋሉ፡፡<br>✓ የተለያዩ የፈጠራ ድርሰቶችን ይገመግማሉ፡፡ |
| **ቅድመ ኮርስ** | - |
| **የኮርስ ምእራፍ ምድብ** | አብይ ኮርስ |

## <u>ዝርዝር ይዘት</u>

ምዕራፍ አንድ፡- የፈጠራ ድርሰት
1.1. የፈጠራ ድርሰት ምንነት እና አስፈላጊነት
1.2. የፈጠራ ድርሰት ባህርያት
1.3. ለምን እንጽፋለን
1.4. የፈጠራ ድርሰት ጸሃፊዎች ተግዳሮት
1.5. የፈጠራ ድርሰት አጻጻፍ ሂደቶች

ምዕራፍ ሁለት፡- የፈጠራ ድርሰት መሰረታውያን
2.1. መጻፍ
2.2.በራስ መተማመንን መገንባት
2..3. አካባቢን መቃኘት
2.4.በራሳችን ልምድ ላይ መመስረት
2.5.የኋላ ታሪካችንን መመልከት
2.6.ማንበብ፣ማንበብ፣ማንበብ

ምዕራፍ ሶስት፡- የፈጠራድርሰት እና የስሜት ሕዋሳት
3.1 በእይታ መጻፍ
3.2. በስሚታ መጻፍ
3.3. በጣእም መጻፍ
3.4.በዳሰሳ መጻፍ
3.5.በሽታ መጻፍ

ምዕራፍ አራት፡- ኢ-ልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰቶች
4.1. ወግ
4.1.1. የወግ ምንነት
4.1.2. የወግ ባህርያት እና እንዴትነት
4.2. ስለራስ መጻፍ (አውቶ ባዮግራፊ)
4.2.1. ምንነት
4.2.2. ዘዴዎች
4.3. ስለ ሰዎች መጻፍ (ባዮግራፊ)
4.3.1. ምንነት
4.3.2. ዘዴዎች

ምእራፍ አምስት፡-ልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰቶችን መጻፍ
5.1. የልቦለድ ዘውጎች እና የፈጠራ ድርሰት
5.2. የልቦለድ ፍሬ ነገሮችን ምንነት እና እንዴትነት

| | ዝርዝር ነጥቦችና ተግባራት |
|---|---|
| በኮርሱ የሚጠበቁ ነገሮች | • ዝግጅት፡-በየቀኑ ክፍል ከመገኘት ባሻገር ከላይ ባለው የትምህርት ቅደም ተከተል መሰረት ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ መምጣት ያስፈልጋል:: <br> • ተሳትፎ፡- የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ቅኝት ትምህርት በሚገባ ማንበብን ይጠይቃል:: ይህም በመሆኑ ሁሉም ተማሪ እዚህ ላይ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌሎች የሥነጽሑፍ እና የታሪክ ስራዎችን በስፋት በማንበብና በማዘጋጀት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል:: |
| ፖሊሲ | - ስም ጥሪ፡- በየክፍለጊዜው የስም ጥሪ ፊርማ የሚኖር ሲሆን በመንፈቅ አመቱ ከ20% በላይ የሚቀር ትምህርቱን መከታተል አይችልም:: |

- መልመጃዎች፡- በየጊዜው በመምህሩ የሚሰጡ መልመጃዎች ክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ሲሆን እነዚህን መልመጃዎች በመስራት ትምህርቱን ማጠናከር እንዲሁም ለፈተና መዘጋጀት ይገባል::
- ምዘናዎች፡-በቡድንና በግል የሚሰሩ ምዘናዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚሰጡ ሲሆን ምዘናዎቹን በጊዜው መውሰድ ላልቻለ ተማሪ የማካካሻ ምዘና አይሰጥም:: ምዘናዎቹም 50% ያህል ዋጋ ስላላቸው ተከታትሎ መውሰድ ይመከራል::
- ፈተናዎች፡-በመንፈቅ አመቱ የሚኖረው የማጠቃለያ ፈተና 50%ዋጋ ይኖረዋል::
- የማማከሪያ ሰዓት፡-ከላይ በተጠቀሰው የማማከሪያ ሰአት መጠቀም የሚቻል ሲሆን የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ ቀጠሮ ወስዶ ከማማከሪያ ሰአት ውጭ ማነጋገር ይቻላል::
- ኩረጃ፡-ኩረጃ ፈጽሞ የተከለከለ ነው::የትኛውም በኩረጃ የተገኘ ውጤት ዋጋ አይኖረውም::የሌላ ሰው ሀሳብን ምንጭ ሳይጠቅሱ መውሰድም ኩረጃ ውስጥ ይጠቃለላል::

**ዋቢ ጽሑፎች**

References


ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ 1999፡፡ *የአማርኛ ስነ ግጥም፡፡* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚ>ች፡

ተስፋዬ አበራና አንተነህ አወቀ፡፡ 1994፡፡ «የአማርኛ ሀተታ ልቦለድ»፡፡ የትምህርት መሳሪያች ማከፋፈያና ማምረቻ ድርጅት፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ አዲስ አበባ፡፡

አማረ ማሞ፡፡ 1986፡፡ *የልቦለድ ድርሰት አጻጻፍ፡፡* (ሦስተኛ እትም) አዲስ አበባ፤ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡

ደበበ ሠይፉ፡፡ 1973፡፡ *የቲያትር ጥበብ፡፡* አዲስ አበባ፤ ንግድ *ማተሚያ* ቤት፡፡

ዳኛቸው ወርቁ፡፡ የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡ 1977፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የሥነ-ጽሑፍ መሰረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡ 1992፡፡

Abrams, M. H. A Glossary of Literary Terms. 4th ed. New York: Rinehart and Winston, 1981.

Casterton, Julia. 1986. *Creative Writing: A Practical Guide*. Hong Kong: Macmillan Education Ltd.

Colins, Sue. 1993. *Approaching Literature*. Great Britain: Cox and Wyman Ltd.

Dianne, Doubtfire. Creative Writing. Berkshire: Cox and Wyman Ltd., 1996.

Erika, Baker. 1992. “Autobiography”. *The World Book Encyclopedia*. Volume A.

Feinberg, Leonard. Introduction to Satire. Ames, Iowa: The Iowa state University Press, 1967.

Gordon Jane Bachman and Kuehnew Karen. 1999. *Fiction: An Introduction to the Short Story.* USA: NTC/Contemporary Publishing Group, Inc.

Gready’ Paul. 1993. “Autobiography and the 'Power of Writing': Political Prison Writing in the Apartheid Era”. *Journal of Southern African Studies*, Vol. 19, No. 3. (Sep., 1993), Pp. 489- 523.

Kleiser, Grenville. The art of writing. New Delhi: APH Publishing, 2004.

Michale, Legat. London: Robert Hall., 1986.

Neumann, Joseph K. 1985. “Diary Writing As a Means to Increased Self-Evaluation”. *Journal of Subsronce Abuse Treatment, Vol. 2, Pp. 221-223*

Osborne, Brian D. 2004. *Writing Biography and Autobiography*. USA.

Pakhare, Jayashree. 2007. How to write a biography. Retrieved on December 11, 2007 from http://www.buzzle.com/articles/how-to-write-a-biography.html *Creative_Writing*. 2008. Retrieved on January 02, 2008

Quinn, K. How literature works. London: Macmillan Press Ltd., 1992.

Sandam, John. 1992. *The Writing Autobiography: Where to begin in a two-year college writing course.* A paper presented at the annual meeting of the conference on college

Tyson, Lois. 1999. Critical Theory: Auser-Friendly Guide: New York &Francis & London: Garland Publishing, Inc.

Verdonk, Peter. Stylistics. New York: Oxford University press, 2002.

Webster, Roger. 1990. *An Introduction Studying Literary Theory: An Introduction*. United Kingdom: Athenaeum Press Ltd.

Wellek, Rene and Austin Warren. Theory of Literature. New York: Harcout, Brace, 1956

## 1 Survey of Ethiopian Literature (ELAm2094) Guide Book

| | |
|---|---|
| Program | Bachelor of Arts in Ethiopian Language(s) & Literature - Amharic |
| Module Title | Fundamentals and survey of ethiopian literature |
| Module Code | ELAm-M2091 |
| Course Title | Survey of Ethiopian Literature |
| Course Code | ELAm 2094 |
| Course credit | 5 ECTS/ 135 hrs |
| Pre-requisite(s) | - |
| Course status | Compulsory |
| Medium of instruction | Amharic |
| Course Chair | Office :<br>Email:<br>Mobile No. |
| Instructor | ………………………… |
| Instructor’s Contact Information | Office Phone Email<br>Office hour |
| Target Group | Year II ,Semester II |
| Mode of delivery | Classroom contact/Lecture, group work, (group and pair work/discussions and individual work (independent learning). |

| Student Work Load (per week) | Gaped Lecture | Tutorial | Group Work & Individual Work | Home Study | Total |
|---|---|---|---|---|---|
| | 48hrs | 0 hrs | 45 hrs | 42hrs | 135hrs |
| Course Description | The course mainly deals with the following major themes: Origin and development of Ge’ez and Amharic alphabet, the origin and development of Amharic Literature, the panegyric poems of the six Ethiopian kings, factors for the rise and /or fall of Amharic Literature in early periods, the emergence of Amharic fictional Literature, major works and prominent writers in Amharic Literature.<br>Within the above frameworks, this course concentrates on Ethiopian literature written in Amharic and other languages in the various times. The origin and development of Ethiopian literature in Amharic, the characteristics and the major thematic preoccupation, the literary, social, cultural and political significances of the works of different writers and the major discourses will be dealt. | | | | |

| | |
|---|---|
| Key Topics | 1. Origin and development of Ge’ez and Amharic alphabet,<br>2. the origin and development of Amharic Literature,<br>3. factors for the rise and /or fall of Amharic Literature in early periods,<br>4. the emergence of Amharic fictional Literature;<br>5. major works and prominent writers in Amharic Literature |
| Course objective and competences to be acquired | 1. Give explanation about the origin and development of Geez literature<br>2. Explain the origin, development, content, basic characteristics of Amharic literature<br>3. Identify prominent literary works and writers in Amharic Literature<br>4. Give logical explanation about the contributing factors for the rise or/and fall of Amharic Literature<br>5. Identify and describe the major forms of Amharic oral literature.<br>6. Discuss mode of communications in oral literature.<br>7. Explain the social function of oral literature.<br>8.Explain and identify the study of oral literature in Ethiopia |

**Course Schedule**

| Week | Topics and Sub Topics | Required Texts |
|---|---|---|
| 1 | Unit one: Origin and development of Ge’ez and Amharic Alphabet<br>Unit two: Surveying Ge’ez Literature | “አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ”<br>“ አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ቅኝት” |
| 2 | Unit three: The birth of Amharic Literature from 14th C. to 17th C.<br>1.1 The Amdetsion Period<br>1.2 The Jesuits period<br>Unit four: Amharic literature during the reign of Tewodrose II<br>1.1 Factors Contributing for the development of Amharic literature during the period<br>1.2 Prominent writers and their works during the period | “አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ”<br>“ አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ቅኝት” |
| 3 | Unit five: Amharic literature during the reign of Menilik II<br>1.1 Amharic Literature in the late 19th C.<br>1.2 Amharic Literature in the beginning of 20th c.<br>1.3 Factors contributing for the development of Amharic Literature during the period<br>1.4 Prominent writers and their works during the period | “አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ”<br>“ አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ቅኝት” |
| 4 | Unit six: The modern Amharic Literature during Emperor Haile Sillasie I<br>6.1 In the1920’s<br>6.2 During Italian occupation<br>6.3 After the Italian occupation | “አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ”<br>“ አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ቅኝት” |
| 5 | 6.4 Factors contributing for the development of Amharic Literature during the period<br>6.5 Prominent Amharic writers and their works during the period | “አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ”<br>“ አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሁፍ ቅኝት” |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | Unit seven: The Ethiopian Literature from 1967 - 1983 E. C.<br>7.1. Major literary trends<br>7.2 The Prominent writers and their works during the period<br>7.2.1 In poetry<br>7.2.2 In Fiction (novel and short story)<br>7.2.3 In Drama | የአማርኛ ልቦለድ ጉዞ፤ መድበለ ጉባኤ (አስፋው ዳምጤ)<br><br>Black Lions (Molvaer R. ) |
| 7 | Unit eight: The Ethiopian Literature since 1983 E C.<br>a. Major literary trends<br>b. The Prominent writers and their works during the period<br>i. In poetry<br>ii. In Fiction (novel and short story)<br>iii. In Drama | |
| 8 | Unit Nine: The Ethiopian Literature in other Languages<br><br>FINAL EXAM | |

Teaching Methods

1. Lecture
2. Reading
3. Review
4. Presentation
5. Classroom exercises
6. Peer and Group discussions
7. field trip

Assessment

1. Term papers (Individually and in groups (20%)
2. Presentation (10%)
3. Quizzes (10%)
4. Field Trip Report (10%)
5. Final examination (50%)

Policy

ATTENDANCE: Students who attend class regularly will increase their chances of success in this course. Accordingly, attendance will be taken at the beginning of each class meeting.
If a student absents more than 20%, he/she advised to withdraw, if not the course grade will be automatically changed to F.

Plagiarism: is a serious form of academic dishonesty. Therefore, it is forbidden .If so happened, the first instance of plagiarized work will receive a grade of zero (0).Any such occurrence thereafter will result in receiving F for the course.

SEEKING HELP: the instructor is available during office hours and by appointment to discuss Readings, ideas, and drafts. Never be afraid to ask questions; never be afraid to ask for assistance.

Disability: If any student has physical, psychiatric, or learning disabilities, he/she has to let the instructor know immediately. In order to make the teaching learning process successful

## References

2.1

Derje Melaku. "The State of Children's Literature in Amharic." Addis Abeba University, SGS. 1994. (MA Thesis)

Gadisa Birru. "Major Features of Conflict in Ten Post 1974 Amharic Short Stories." A.A.U., SGS. 1994. (MA Thesis)

Getachew Sahilemariyam. "A Study of Some Major Characters and Themes in Post Revolution Amharic Novels." A.A.U., SGS. 1985. (M.A. Thesis.)

Hussein Ahmed. 1998. "Islamic Literature in Ethiopia: An Overview". *Ethiopian Journal & Languages and Literature*. Institute of Language Studies, A.A.U. 1998.

Kane, Thomas L. Ethiopian Literature in Amharic. Otto Harrassowitz, Wiesbaden, Germany. 1975.

Melese Taddese."Thematic Trends of Poems in Selected Amharic Magazines (1956-1995)." A. A.U., SGS. 1996.

Meseret Abeje."Major Themes in Post 1970 EC. Amharic Short Stories". A.A.U., SGS. 1992. (MA Thesis.)

Molvaer R. Black Lions; the Creative Lives of Modern Ethiopia’s Literary Giants and Pioneers. The Red Sea Press Inc., Asmera; Eriteria. 1996

Molvaer, K. Reidulf. 1980. *Tradition and Change in Ethiopia Social and Cultural Life as Reflected in Amharic Fictional Literature* (1930-1974). Leyden.

Taye Assefa. 1986. "Form in the Amharic Novel". Ph. D.

Teferi Nigussie. "Development of Oromo Literature up to 1991." A.A.U., SGS. 2006. (MA Thesis)

Zelalem Getahun. "Amharic Political Plays (1974-1981)" Addis Abeba University, SGS. 1997. (MA Thesis)

አስፋው ዳምጤ:: (2001)፡፡ የአማርኛ ልቦለድ ጉዞ፤ መድበለ ጉባኤ

አምሳሉ አክሊሉ፡፡ 1976 «የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ቅኝት»፡፡ ያልታተመ፡፡

አስፋው ዳምጤ፡፡ 1984፡፡ «አንዳንድ ነጥቦች ስለ አማርኛ ጥበበ ቃላት»፡፡ *ጦቢያ መጽሔት* ልዩ እትም፡፡

አንተነህ አወቀ እና ማስተዋል ውበቱ፡፡ 1997፡፡ «የአማርኛ ስነጽሁፍ ቅኝት(ቁሮቂ.112) ሞጁዩል»፡፡ ባህር ዳር፤ ባሃር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

አንተነህ አወቀ፤ 2001፡፡ ‹ የአማርኘ ስነጽሁፍ ባሳለፍነው ሚሊኒየም› ፤ የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ

«ያማርኛ ልቦለድ እድገት ከጦቢያ እስከ አደፍርስ» *ብሌን ቁጥር 1*

ይልማ ከበደ፣ 1982፣ "ስነግጥም 1307-1933" በስቴንስል ተርጾ የተባዛ፡፡ አ.አ.ዩ፡፡

ዮናስ አድማሱ፣እና ሌሎችም፡፡ 1966፡፡ «አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ»፡፡ አዲስ አበባ፤ ቀ.ኃ.ስ.ዩ.(በስቴንስል የተባዛ)፡፡

ዮሃንስ አድማሱ፣ 1990፣ *እስኪ ተጠየቁ*፡ አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርኘራይዝ፡፡

ዮሃንስ አድማሱ፡፡ 1961፡፡ «የልቦለድ ስነጽሑፍ ጉዞ»፡፡ *የካቲት መጽሄት* 1980፡፡ እና *ብሌን* ቁጥር 2 1994፡፡ ቁ. 11 እና 12፡፡

ደበበ ሰይፉ፡፡ 1974፡፡ «የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እድገትና አቅጣጫ» *የካቲት መጽሄት፡፡* ቅጽ 5 ቁ. 4፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1986፡፡ "የአጭር ልቦለድ ኪነጥበብ ጥቂት ገጽታዎች እና ሌሎች 11 ስነጽሁፋዊ መጣጥፎች"፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1999፡፡ «ቀደምት የአማርኛ አጭር ትረካች ምንነትና አበይት ባህሪያት»፡፡ *የኢትዮጵያ ጥናት መጽሄት፡፡* ቅጽ. 32 ቁጥር 2፡፡

ፋንታሁን እንግዳ፡፡ 1994፡፡ «ቀደምት የአገራችን የተውኔት ድርሰቶች ከርዕስ አሰጣጥ አንፃር ሲታይ»፡፡ የቋንቋች ጥናት ተቋም አስራ ሰባተኛው ዓመታዊ ጉባኤ የቋንቋት ጥናት ተቋም አ.አ.ዩ፡

Approval

| | Instructor Name | Course Chair | Department Head |
|---|---|---|---|
| Sign | ___________ | _______________________ | |
| Date | _______________________________ | | |

# የፈጠራ ድርሰት አውደ ጥናት (Workshop on Creative Writing )

## ደራጎት/ማስታወሻ

## አዘጋጅ ምስራቅ ጠና

## ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

ብዙ ሰዎች የፈጠራ ድርሰትን የተወሰኑ ሰዎች መክሊት አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ ይታይባቸዋል፣ የብዙ የቋንቋ ተማሪዎች አመለካከትም ከዚህ የተለየ አይደለም። ውድ ተማሪዎች እንደ ሌሎች ክህሎቶች ሁሉ የፈጠራ ድርሰት ከተሰጥኦ በተጨማሪ የልምምድ/ጥረት ውጤት ነው። ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች ቢሆኑም እንኳን ብዙ ካልጣሩ( ብዙ ካላነበቡና የጽህፈት ልምምድ ካላደረጉ) ውጤታማነታቸው አጠራጣሪ ነው። በመሆኑም የፈጠራ ድርሰት አጻጻፍ አውደ ጥናት የተባለው ትምህርት የሚሰጠው የድርሰት ክህሎት በተሰጥኦ ብቻ የሚገኝ አለመሆኑን ለማስገንዘብና እናንተ ተማሪዎችን ከተለያዩ የፈጠራ ድርሰት አሰተሳሰቦች እና የፈጠራ ውጤቶች ጋር በማሰተዋወቅ፣ የተለያዩ ዘዴዎችና ቴክኒኮች በማስተማር እንዲሁም በተለያዩ በደረጃ ሂደታዊ ስልቶች የፈጠራ ድርሰት ችሎታችሁን እንድታወጡና እንድታዳብሩ ለመርዳት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የፈጠራ ድርሰትን መማር እና ተግባራዊ ማድረግ ሰፋ ያለ ጠቀሜታ አለው። እነዚህም፡-

1. ተማሪዎች ሃሳባቸውን በተሻለ እና በማያሻማ መንገድ እንዲገልጹ ይረዳቸዋል።
2. የተለያዩ ነገሮችን ከተለመደው መንገድ ወጣ ብለው እንዲመለከቷቸው እና እንዲመረምሯቸው ያግዛል።
3. ምናባቸውን በማንቃት ሃሳባቸውን በራሳቸው መንገድ እንዲገልጹ ያስችላቸዋል።
4. የፈጠራ ድርሰትን መማር ከተለያዩ ስነጽሁፋዊ ዘዴዎችና አላባዎች ጋር ስለሚያስተዋውቅ የተማሪዎችን ቋንቋ የመጠቀም አቅም ያሳድጋል።
5. የተለያዩ ነገሮችን በጥልቀት እና አመክንዮን መሰረት አድርጎ የመመልከት ልምድን ያሳድጋል።
6. ችግር የመፍታት ብልሃትን ያዳብራል።

## 1.1 የፈጠራ ድርሰት ምንነት

የፈጠራ ድርሰት ስለተለያዩ ሁነቶች ወይም አጋጣሚዎች ምናባዊ በሆነ መንገድ በጽህፈት ለአንባቢ ማቅረብ ነው፡፡ አንድ ጸሃፊ ያጋጠሙተን ነገሮች ወይም የተሰማውን ነገር በምናቡ አርቅቆ፣ ስሎ፣ አጥልቆ፣ አጉልቶ፣ አኮስሶ፣ አስፍቶ፣....ባልተለመደ መንገድ የተለያዩ [1]ድምጸቶችን አላብሶ በጽ ህፈት የሚያቀርበው ጥበባዊ አንጸባርቆ የፈጠራ ድርሰት ይባላል፡፡ይህ ጽሁፍ ልቦለዳዊም ሆነ ኢ-ልቦለዳዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ዓላማውም ከሃሳብ እና ስሜት ጋር የተያያዘ የሆነ ነገርን መግለጽ ነው፡፡ ለአንባቢው መረጃ ከመስጠት ወይም ጸሃፊውን የሚጠቅም ወይም የሚፈልገውን ተግባር እንዲያከናውን ከማድረግ ይልቅ የፈጠራ ድርሰት የሚጻፈው ለማዝናናት፣ ስለተለያዩ ጉዳዮች ለማሳወቅ ወይም ሃሳብን ለመግለጽ ነው፡፡

የፈጠራ ጽሁፍ ከሙያዊ፣ጋዜጣዊ፣ትምህርታዊ እና ቴክኒካዊ ጽሁፎች ውጭ ያሉ ማናቸውንም ልቦለዳዊ እና ኢ-ልቦለዳዊ ጽሁፎች ይመለከታል፡፡ ሙያዊ፣ጋዜጣዊ፣ትምህርታዊ እና ቴክኒካዊ ጽሁፎች ምድባቸው ከኢ-ልቦለድ ሲሆን የተከሰቱ ወይም እየተከሰቱ ያሉ ሁነቶችን፣ሊደረጉ የሚገቡ ጉዳዮችን፣የአሰራር መመሪያ እና አጠቃቀሞችን ያለ ምንም ጭምርማሪ እና ማጣፈጫ ወይም የስሜት ማማለያ በመረጃ ላይ ተመስርተው የሚያቀረቡ መደበኛ የጽሁፍ አይነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የጽሁፍ አይነቶች ለማሳወቅ እና ለማስተማር እንጂ ለማዝናናት ተብለው የማይጻፉ የተለያየ ቅርጽ እና የአጻጻፍ ስልት ያላቸው ለተለያዩ የሙያ መስኮች ግልጋሎት የሚሰጡ የጽሁፍ አይነቶች ናቸው፡፡

ነገር ግን የፈጠራ ድርሰት የሚጻፈው ለማዝናናት ነው፡፡ ግጥም እና ልቦለድን የምናነበው ስለሚያዝናኑን እንጂ በቀዳሚነት ስለሚያስፈልጉን ወይም ስለሚረዱን አይደለም፡፡

በፈጠራ ድርሰት አንድ ባዶ ገጽ እንደ አንድ ክፍት ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ግን እንደ ግኡዙ ወረቀት በወርድና በስፋት የተገደበ አይደለም፡፡ የፈለግነውን መልከአምድራዊ፣ ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ሰባዊ ቀለም ልናፈስበት እንችላለን፡፡ በዚህ ስፍራም የጊዜ ገደብ የለም፤ የፈለግነውን ሰአት፣ ቀን፣ ወቅት፣ አመት፣ ዘመን ወዘተ ልንቀርጽበት እንችላለን፡፡ ሁሉም ነገር ይቻላል፡፡ ያለምንም ገደብ ምንም ነገር እዚህ ስፍራ ሊበቅል ይችላል፡፡ ማንኛውም አካል እውናዊም ሆነ ምናባው በዚህ

---

[1] ድምጸት የምንለው ጽሁፎች የሚሸከሙትን ስሜታዊ ሁኔታዎች ነው፡፡ ለምሳሌ የማስፈገግ፣ የማስለቀስ፣ የመዘግንን፣ የማስደንገጥ፣ የመጨፍገግ፣ድንቃይ፣ ቧልታይ፣ ወዘተ...

ስፍራ ሊዘዋወር ይችላል፡፡ በዚህ ስፍራ ገደብ ሊያበጁ የሚችሉት የጸሃፊው ሃቀኝነት እና የምናብ ወሰን ናቸው፡፡ የተወለድንበት ሁኔታ ከዚህም ያዳበርነው ባህሪ እንቅፋት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሃብታም እንሁን ደሃ፣ ሃይማኖተኛ እንሁን አለማዊ፣ ፈጣን እንሁን ረጋ ያልን ካልዋሸንና ካላዳለን የፈጠራ ድርሰታችን ውጤታማ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የምናባችን ወሰን ማለተም በምንጽፈው ጉዳይ ላይ ያለን እውቀት እና ከስነጽሁፋዊ ስልት ጋር በተያያዘ ያለን ልምድም እንዲሁ የፈጠራ ድርሰታችን ላይ ተጽእኖ ያዳብራሉ፡፡

በፈጠራ ድርሰት ክፍቱ ቦታ ሰዎች በጸሃፊው አማካኝነት የሚወለዱበት ወይም የሚሰሩበት ነው፡፡ እዛ ክፍት ቦታ ላይ አንድ ሙሉ አለም ልንቀርጽ፣ ብዙ ዓለማትን ልናዋድድ ወይም ትይዩ ሁለንተና (Universe) ልንቀርጽ እንችላለን፡፡ በሁለንተና ያለ ማንኛውም ሁኔታ ሊቀመጥ የሚችለው አራት ጎን ባለው የቦታ እና የጊዜ ወለል ላይ ነው፡፡ ጽህፈት በቦታ እና ጊዜ ስርአት ለአንባቢው ቅቡል የሆኑ ግላዊ ሁለንተናዎችን የመፍጠር አቅም አለው፡፡ አንባቢውም የሁለንተናው የጋራ ፈጣሪ ነው፡፡ ቦታ-ጊዜውን እውን ለማድረግ የአንባቢውን እና ጸሃፊውን ትብብር ይጠይቃል፡፡ አንባቢዎች ይሳተፋሉ በከፊል ጸሃፊ ይሆናሉ፡፡ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በፈጠራ ድርሰቱ ሂደት ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ህይወታቸውንም በዛ ቅጽበት እና ፍጥነት ይኖሩታል፡፡ ደራሲው ቃላትን ይሰራል.....አንባቢው ስእልን ይፈጥራል፡፡ የፈጠራ ድርሰት ከእውናዊው አለም ጋር ትይዩ የሆኑ አዳዲስ አለማትን እናሊሆኑ የሚችሉ ሁለንተናዎችን ስለሚፈጥር ሰዎችን ይቀይራል፡፡ የፈጠራ ድርሰት የህይወት ምሳሌን ያቀርባል፡፡

## 1.2. የፈጠራ ድርሰት ባህርያት

1. ውስጣዊ ስሜትን እና ፍላጎትን ለመግለጽ ያስችላል፡፡

የፈጠራ ድርሰት ከላይ እንደተመለከትናቸው የጽሁፍ አይነቶች የይዘትም ሆነ የቅርጽ ገደብ የለበትም፡፡ ጸሃፊው ሊያካፍል የፈለገውን አጋጣሚ ወይም ጉዳይ በነጻነት ማስተላለፍ ይችላል፡፡ ሰው ምን ይለኛል ወይም ይህ ጉዳይ ለንባብ አይሆንም ብሎ ማሰብ የለበትም፡፡ የተሰማውንና መግለጽ የፈለገውን ነገር በሃቀኝነት እና ያለ አድልኦ መግለጽ ይችላል፡፡

2. ለመፍጠር ቦታ፣ጊዜ እና ገጠመኝ ይፈልጋል፡፡

ይህ የፈጠራ ድርሰትን ለመበየን የሚሞክሩ ምሁራን ከሚገጥማቸው ሙግት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህም ፈጠራ የሚባል ነገር አለ ወይ? ከሚለው ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ደራሲ ያለውን ነገር

በድጋሚ ያሳያል እንጂ ከየት አምጥቶ ይፈጥራል የሚል ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። ለዚህ ምላሹም አዎ ደራሲ የተለየ ሙሉ ነገር አይፈጥርም፤ የነበረውን፣ያለውን፣ ወደፊት ይሆናል ብሎ የተነበየውን ግን አዲስ በሆነ መንገድ ትኩስ አድርጎ ያቀርብልናል። ከነበረው ነገር ተነስቶ በአስተማስሎ ያቀርብልናል። አስተማስሎ ማለት መመሰል፣መከየን፣መቀረጽ፣ መሳል፣ማስመሰል፣ ማዋቀር፣ ማሳየት፣ መንገር፣ መተረክ፣ ወዘተ ማለት ነው።

በአስተማስሎ ንድፈ ሃሳብ መሰረት፣ደራሲው የአሰተማስሎ አቅጣጫ ሚያተኩረው ተፈጥሮን መመሰል ወይም ማንጸባረቅ ላይ ነው። በመሆኑም ሰው በተፈጥሮው ከአለም የተገነዘበውን የራሱን ስልት ጨምሮ መልሶ ለአለም ያወርሰዋል።ለዚህ ነው ፈጠራ ድርሰት ጸሃፊዎች አጋጣሚ ይሻሉ የምንለው። ስለማናውቀው ነገር መጻፍ ስለማይቻል።

3. ገለልተኛ ያልሆነ ድምጸት አለው።

የተለያዩ ስሜታዊ ሁኔታዎችን አንባቢዎች ላይ ይፈጥራል።ድምጸት የምንለው ጽሁፎች የሚሸከሙትን ስሜታዊ ሁኔታዎች ነው። ለምሳሌ የማስፈገግ፣ የማስለቀስ፣ የመዘግንን፣ የማስደንገጥ፣ የመጨፍገግ፣ድንቃይ፣ ቧልታይ፣ ወዘተ…

4. ወጥ ነው

ይህ የፈጠራ ድርሰት የራሱ የሆነ ቅርጽ እንዳለው የሚያመላክት ባህሪ ነው።

5.ቋንቋው የስነጽሁፍ ነው።

ይህ የፈጠራ ደርሰት በቋንቋ እንደሚጫወት የሚያመላክት ባህሪ ነው።

## 1.3. ለምን እንጽፋለን?

1. ጽህፈት ምንም እንኳን እንድናተኩር፣ እንድንመሰጥ እና አንድንለፋ ቢያደርግም የተሻለ ህይወት አንዳለን  እንዲሰማን እና እንድንደሰት ያደርጋል። መጻፍ የተለያዩ ጉዳዮችን በተሻለ መንገድ፣ በግልጽ እና በስፋት እንድናስብ፣  እንድንመረምር እንዲሁም እንድንረዳ ያግዛል። ስለራሳችንም ሆነ ስለሌሎች የተሻለ እይታ እንዲኖረን ያደርጋል።

የጽህፈት ሂደት አንድ ቦታ ላይ ሃሳባችንን እንዲረጋ ሲያደርግ በተመሳሳይ ሃሳባችንን ሊበታትንም ይችላል፣ ይህም ሂደት ሱስ ይሆናል። ካለቀው ስራ ይልቅ ሂደቱ አርኪ ነው።

2. የጽህፈት ሂደትን ብዙዎች የህክምና መንገድ አድርገው ይመለከቱታል። ምንም አንኳን መጻፍ በራሱ ሙሉ ለሙሉ ፈዋሽ ባይሆንም ብዙ ጸሃፊዎች ተግባሩን እንደ ህክምና ሂደት (ቴራፒ) ይመለከቱታል። ግለሰቦች የሚገጥማቸውን ድባቴ (ዲፕረሽን) ከማከም ማህበራዊ ማገገሚያ እስከመሆን ያገለግላል። መጻፍ ይቀሰቅሳል። ከምናስበው በላይ ሃይል ይሰጠናል። ከእለት ተእለት ልማዳችን አናጥቦ ይገፋናል።

3.የፈጠራ ድርሰትንም የራስ ሙያ ለማድረግ ልንጽፍ እንችላለን።

4. ፈጠራ ድርሰት ለቅረሳ ሊጻፍ ይችላል። የተለያዩ ገጠመኞቻችንን እና ሃሳቦቻችንን ዘመን ተሻጋሪ ሆነው እንዲቆዩ በሚፈጠር ፍላጎት የፈጠራ ድርሰት ልንጽፍ እንችላለን።

5. አንዳንድ ጸሃፊዎች እውቅናን ዝናን በመሻት ሊጽፉ ይችላሉ።

# የፈጠራ ድርሰት መሰረቶች

## 1. መጻፍ

በፈጠራ ድርሰት የመጀመሪያው ህግ **ጸሃፊዎች መጻፍ አለባቸው** የሚለው ነው። የፈጠራ ድርሰት ጸሃፊ በየቀኑ አንድ ነገር መጻፍ አለበት። ምንም አንኳን የጽሁፉ መጨረሻ ቆሻሻ መጣያ ቢሆንም እንኳን እለት እለት መጻፍ አለበት።

መጻፍ በምንፈልገው ዘርፍ ወደፊት ውጤታማ እንድንሆን በየቀኑ መጻፍ ዲስፕሊን እና ዝግጁነት እንዲኖረን ያደርጋል።

እንደ ጸሃፊ ለራሳችን ለመጻፍ ፍቃድ ልንሰጥ ይገባል።ዝነኛ ስላልሆንኩ ተቀባይነት አይኖረኝም ከሚል ፍራቻ እራሳችንን አላቀን ለመጻፍ ያለን ፍላጎት እውነተኛ እንደሆነ እራሳችንን ማሳመን አለብን። ይህ ሊያሳስበን አይገባም ታወቂ የምንላቸው ደራሲዎችም ቢሆን የጀመሩት ከሆነ ቦታ ነው። ስለዚህ በውጫዊ ግፊቶች ተጽእኖ ስር ልንወድቅ አይገባም። ሁል ጊዜ መጻፋችን ከሌሎች ተግባራት የተሻለ አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ አለብን።

## 2. በራስ መተማመንን መገንባት

ለጀማሪ ደራስያን ትልቁ እንቅፋት በራስ የመተማመን ችግር ነው። ይህ ቀላል ችግር አይደለም ነገር ግን ከልብ መጻፍ ከፈለግን **ሌላ መንገድ የለም ያለብን መጻፍ ነው።**

ሳለመጻፋችን ብዙ ጊዜ በምክንያትነት የምናስቀምጠው ጊዜ ማጣትን ነው፡፡

- የሙሉ ጊዜ ስራ አለኝ
- ቤተሰቤ ብዙ ነው
- ብዙ ሌሎች ሃላፊነቶች አሉብኝ
- በጣም ደክሞኛል

እነዚህ ሁሉ ሰበቦች ወደ አንድ ምክንያት ሊጠቀለሉ ይችላሉ፡፡ **ጥሩ እንደሆንን እራሳችን አላመንም፡፡** የሚከተሉት ሂደቶች ሊያግዙን ይችላሉ፡፡

1. የምንጽፍበትን ቦታ ለይቶ ማዘጋጀት
2. ሁልጊዜ ሃሳባችንን የምናሰፍርበት ማስታወሻ ደብተር መያዝ
3. ለመጻፍ የሚመቸንን ሰአት መለየት እና እሱን መከተል፡፡
4. ለምንጽፍበት ጊዜ መመደብ፣ በቀን/በሰአት
5. በየቀኑ የሆነ ነገር መጻፍ እና እስከሚቀጥለው ቀን ማቆየት፡፡ መጻፍ ስንጀምር ቀድመን የጻፍነውን በማንበብ መጀመር፡፡
6. በአቅራቢያችን መዝገበ ቃለት ማኖር፡፡

## 3.አለምን/ አካባቢያችንን መቃኘት

ጻሃፊ እንዳንዷን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ በጸሃፊ አይን ማየት አለበት፡፡ ለጽሁፉ ግብአት የሚሆነው ይህ ስለሆነ

በቀን ተቀን እንቅስቃሴ ውስጥ ሰዎች ምን አይነት ባህሪ እንደሚያሳዩ፣ ምን እንደሚተገብሩ መመልከትን ማሰታወሻ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌ

- ወደ ምግብ መመገቢያ አዳራሾቻችን ስንሄድ የሌሎች ተማሪዎችን ባህሪ መመልከት፡፡
- መማሪያ ክፍል፣ ቤተመጻህፍት……….. ስንሄድ የሌሎች ተማሪዎችን ባህሪ መመልከት፡፡

    ከተማሪዎቹ ገር ጥቂት ማውራት፡፡ ስለሚያወሩት ነገር ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚያወሩም መመልከት፡፡

- ወደስራ ቦታችን ስንሄድ አብረውን የሚጓዙ መንገደኞችን ለማጥናት እንጠቀምበት፡፡ ከምን አይነት ቤት እንደሚወጡ፣ ምን አይነት ኑሮ እንደሚኖሩ በምናባችን ለመሳል እንሞክር

**መመልከት ብቻ ሳይሆን ማዳመጥም ይገባል፡፡ ደራሲዎች ያለምንም ሃፍረት የሰዎችን ግላዊ ንግግሮች የሚያደምጡ ናቸው፡፡**

ከጸሃፊ ግሩም ተበጀ የፌስቡክ ገጽ(ጁላይ 21፣2018 ጎ.አ) የተገኘው ጽሁፍ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡-

*መቼ ለታ ታክሲ ውስጥ ያጋጠመኝ ነው - መጨረሻው ወምበር ላይ እናት አባት ልጅ ተቀምጠዋል - የአብይ ፎቶ ታክሲው መስኮት ላይ ተለጥፏል፡፡ አብይ ወደ ኋላ ቀለስ ብሎ በደስታ ይስቃል - እኔ ቀጣዩ ወምበር ላይ ነው ያለሁት፡፡ ድንገት ጸጥ ባለው ታክሲ ውስጥ ልጁ አባቱን ጠየቀው፣*

*"አባ … ግን አንተ ለምን እንደ አብይ አትሆንም ?" ጠላታችሁ ክው ይበል አልል ነገር ዘመኑ የመደመር ነው - ብቻ ክው አልኩላችሁ … አመዴ [ገበያ…]*

*አባት ምን ይበል ድምፁ ጠፋ… [አባቶች ኦሾን ማንበብ እንዳለባቸው የገባኝ ያኔ ነው - "ባቢዬ ማንም ሰው ማንንም መምሰል የለበትም፡፡ ሁላችንም ራሳችንን ነው መሆን ያለብን" ብሎ ልጁን አይመክር ነገር ሚስኪኑ አባት ከየት ያምጣው ይሄን ጥበብ፣ ይሄን ፍልስፍና - አፍሬ ጥፍሬ ውስጥ መግባት አማረኝ - ደግሞ ጥፌሬን ተቆርጬዋለሁ…]*

*ትንሽ ቆይቶ ልጅ ሌላ ጥያቄ አስከተለ - ወደኋላ ዞሬ ልጁን ማየት ፈልጌ ነበር - ግን አፍሬ ተውኩት - ልጁ ቀጠለ - ምናልባት አራት አመት ቢሆነው ነው ከድምፁ እንደምረዳው…*
*"እሺ … ለምን ፂምህን እንደአብይ አትቆረጥም ?"*

*ወይ መአልቲ !!!*
*የኮንዶም ጥቅም ይሄኔ ነው የገባኝ…*

*ምስኪን አባት ምን ይበል - ደምፁን አጥፍቶ ጭጭ…*
*ልጁ ሊያቆም ነው - ሌላ ጥያቄ…*

*"ቆይ ይሄ አብይ ግን ምንድነው የሚሰራው ግን ?"*

*አባት ይሄኔ ተነቃቃ፣ "ያነባል … ይፅፋል … ሕዝብ ይመራል" አለ አባትዬው፡፡ ከሁኔታው አባትዬው ራሱ ቀንደኛ የአብይ አድናቂ መሆኑ ያስታውቃል፡፡ ለነገሩ ማን ያልሆነ አለ - ግን አባትዬው ድምፅ ውስጥ ያለው ስሜት አብይን በጣም እንደሚወደው ያሳብቅበታል…*

*ልጁ የአባቱን መልስ እንደሰማ የተናገረው ነገር ግን ወሽመጤን ቆረጠው፣*
*"እንዴ ታዲያ ይሄ ሥራ ነው እንዴ … ብር እኮ አያስገኝም !!!" ብሎ አረፈዋ ልጁ*
*…*
*ከዛን በኋላ አባት አፈረ መሰል ከእናትየው ጋር ማውራት ጀመሩ፡፡ መስኮቱ ላይ መልከ መልካሙ ጠቅላይ ሚኒስትር ተንጋሎ ይስቃል - አብይ ጉድ አፈላ አልኩኝ፡፡*

*በዛሬ ልጆች ጭንቅላት ውስጥ ያሉ ሁለት ታላለቅ ነገሮች አብይ አህመድ እና ገንዘብ መሆናቸውን ግን ተረድቼ ነው ከታክሲው የወረድኩት…*

## 4.በራሳችን ልምድ ላይ መመስረት

ለጀማሪ ጸሃፊያን የመጀመሪያው ህግ መሆን ያለበት ስለምናውቀው ነገር መጻፍ ነው። "ስለምታውቁት ነገር ጻፉ ካልሆነ ለማወቅ ሞክሩ።" ይህ ርእሰ ጉዳይን ብቻ ሳይሆን ዘውግንም ይመለከታል።

ሁሉም ደራሲ ሁሉንም ነገር አያውቅም ግን መማር ይችላል። ለምሳሌ ከኛ ዘመን ስለቀደመ ጊዜ ለመጻፍ በዛ ዘመን መኖር አይጠበቅብንም። ታሪኮች ላይ ጥልቅ ምርምር በማድረግ መሰረታዊ የሆኑ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል። ይህ ማለት ግን በሁኔታው ውስጥ ማለፍ አስፈላጊ አይደለም ማለት አይደለም። አመታትን በተለያዩ የስራ ዘርፎች /አካባቢዎች/ ማሳለፍ ጥቅም የለውም ማለት አይደለም። እነዚህ ልምዶች ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው የመረጃ ሃብቶች ናቸው። ነገር ግን እውነት የሆነውን ነገር ብቻ ማካበት የጽሁፍ አንድ ጎን ነው።

በታሪካችን ውስጥ ያሉ ገጸባህርያት ላይ ህይወት መዝራት አለብን። ይህ ደግሞ የሚመነጨው ከነበረን ግለሰባዊ ግንኙነት ልምዶች ነው። ገጸባህርያቶችን በመቅረጽ ሂደት ቀዳሚ ከሆኑት የልጅነት ትውስታዎቻችን ጀምሮ የትምህርት ቤት ቆይታችን፣የአዋቂነት፣የጉደኝነት ጊዜያችን፣የፍቅር ግንኙነታችን፣የስራ ልምዳችን፣ የቤተሰብ ህይወታችን ሁሉ አስተዋጾ አለው።

ዘውግም ከዚህ የተለየ አይደለም ለምሳሌ ሁሉም ደራሲ ስለታሪካዊ ሮማንስ፣ ስለድህረ ዘመናዊ ስነጽሁፍ፣ስለ ስነልቦናዊ ስነጽሁፍ ወዘተ. ላያውቅ ችላል ስለዚህ በዚህ ዘርፍ ለመጻፍ ቅድሚያ ስለዘውጎቹ ምንነት እና እንዴትነት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት።

## 5. የኋላ ታሪካችንን መመልከት

በተለምዶ መጻፍ የሚችለው በብዙ የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ያለፈ ሰው እንደሆነ ስለሚታመን ብዙዎቻችን በህይወታችን ያከናወነው ነገር ለወረቀት የሚበቃ አይደለም ብለን እናስባለን። በትኩረት ስንመረምር ግን ይህ ከእውነታ የራቀ ነው። እስቲ እራሳችንን ወደቀደሙት ትዝታዎቻችን እንውሰድና እና ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነገሮች ሲገጥሙን ምን ተሰምቶን እንደነበር እናስብ ።

- ቤተሰቦቻችን ሲጨቃጨቁ
- አስቸጋሪ ስለሆንን ቁጣ ሲደርስብን
- ልጆች ሲያሾፉብን

- ትምህርት ቤት ስንቀጣ
- ታመን ሆስፒታል ስንታከም
- በቤተሰብ ችግር ምክንያት ከእንግዲህ ሁሉም ነገር በቤት ውስጥ ተመሳሳይ እንደማይሆን ሲሰማን
- የአያታችን እቅፍ ውስጥ በክረምት ጊዜ….ወዘተ.

እነዚህ ብዙ ልጆች የሚጋሯቸው ልምዶች ናቸው። እስቲ እድሜያችሁን ትንሽ ከፍ አድርጉትና አስቡ

- ቤት ስትለቁ
- የመጀመሪ ቀን ከትውልድ ቀዬአችሁ ስትወጡ
- የመጀመሪያ ቀን የዩኒቨርሲቲያችሁን ደጃፍ ስትረግጡ
- የመጀመሪያ የሆቴል ቤት ቆይታችሁ
- የመጀመሪ ስልካችሁን ስትገዙ….. ወዘተ.

ተለምዷዊ የሆኑ የእለት ተእለት ልምዶቻችን ለፈጠራ ድርሰት ምን ፋይዳ ይኖራቸዋል ብላችሁ እያሰባችሁ ይሆናል። እውነት ነው መጻፍ ባንክ ሄዶ አካውንት እንደመክፈት ቀላል አይደለም። የፈጠራ ድርሰት ምናባዊ እና ወጥ ሃሳቦችንና እና ያልተለመዱ ሁኔታዎችን የሚመለከት ነው። ደራሲም እነዚህን ሁሉ ተራ የሚመስሉ ገጠመኞቹ ውስጥ በትልቀት ሲመረምር ያገኛል።

ስንጽፍ ለልምዳቸን ስሱ መሆን አለብን። ምንም እንኳን ያለፍንባቸው አጋጣሚዎች ትንሽ ቢሆኑም በጥልቀት በቆፈርን ወይም በመረመርን ቁጥር ጥልቅ የሆኑ እውነታዎችን እናገኛለን። አንዳንድ ሰዎች አለምን ዞረው አሰልቺ ጽሁፎችን ይጽፋሉ አንዳንዶች ሩቅ ሳይሄዱ ምርጥ ጽሁፍ እንካችሁ ይላሉ። አንድን ጽሁፍ ምርጥ የሚያደርገው ጥልቅ ሃሰብና ሃሳቡ የሚንጸባረቅበት መንገድ ነው። ምንም ነገር ትንሽ/ጥቃቅን ነው ተብሎ አይተውም። ሰዎች ትኩረት በማይሰጧቸው ነገሮች እምነት ይኑረን እነዚህ ነገሮች ድንገት ገዘፍ ነስተው የማይለኩ ይሆናሉ።

**ሙከራ፡-** እስቲ በልጅነታችሁ ወይም በጉርምስናችሁ ያለፋችሁበትን አንድ አጋጣሚ አስቡና በወቅቱ የተሰማችሁን ስሜት መነሻ በማድረግ አንድ አጭር ታሪክ ጻፉ።

## 6.ማንበብ፣ማንበብ፣ማንበብ

የምንም አይነት ጽሁፍ ፍላጎት ይኑረን ልቦለድም ይሁን ኢ-ልቦለድ፣ረጅም ልቦለድ ይሁን መጣጥፍ በመረጥነው ዘውግ የምናገኛቸውን ጽሁፎች ሁሉ ማንበብ አለብን፡፡ ብዙ ባነበብን ቁጥር ከሞላ ጎደል በሁሉም ጽሁፎች ተመሳሳይ ህግ እንደሚሰራ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ የመረጥነው ዘውግ አጭር ልቦለድ ከሆነ ብዙ አጭር ልቦለዶችን ስናነብ ለአጭር ልቦለዶች መሰረታዊ የሆኑ የአወቃቀር ብልሃቶችና ቴክኒኮች እንረዳለን፡፡

ጥልቅ እይታችን ሲዳብር የንባብ ፍሰታችን በፊት ባላስተዋልናቸው አንዳንድ ቴክኒካዊ ጉዳዮች ሲደናቀፍ እናስተውላለን፡፡ አዲስ ያገኘነው ክሂልም በጥሩ ሁኔታ የተጻፉ ጽሁፎችን እንድናደንቅ ይረዳናል፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ ስንደርስ የኛም ስራ የሚታይ መሻሻል ይስተዋልበታል፡፡

## 3. የፈጠራ ድርሰት እና ስሜት

ጥሩ ጽሁፍ በስሜት ህዋሳቶቻችን ውስጥ የሚያልፍ ነው፡፡ የፈጠራ ድርሰት ጸሃፊ ልምዱን እየጠቀለለ ማቅረብ የለበትም በስሜት ህዋሳቶቹ ሊያሰፋው ይገባል፡፡ በስሜት ህዋሳቶቻችን አማካኝነት በምናባችን አጋጣሚው/መቼቱ ላይ ከቆየን ጠቅለል አድርገን ያቀረብነው ጉዳይ ስህተት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ብዙ በምናብ በተጓዝን እና በህሊናችን የተለያዩ ምስሎች በተመላለሱ ቁጥር አጠቃለን ባቀረብነው ጽሁፍ ብዙ የሚረብሹ ነገሮችን እናገኛለን፡፡

ምሳሌ አንድ፡-

1."በአባቴ ቤት ውስጥ ያለምቾት ተቀምጫለሁ፡፡" ከምንል ይልቅ አለመመቸትን የሚገልጹ ተጨማሪ ምስሎችን ብናክል የተሻለ ነው፡፡

2. "ደረቅ እና ወፍራም በሆነ ፎም ከተሰራው ሃምራዊ ሶፋ ላይ ተቀምጫለሁ፡፡ እግሮቼ መሬት መንካት ተስኗቸው ተንጠልጥለዋል፡፡ ጉልበቴ ላይ ረግቶ አልቀመጥ ያለኝ ቀሚሴን አስሬ እጎትታለሁ፡፡"

ምሳሌ ሁለት፡-

1. "አባቴ አያቴ እየሞተች እንደሆነ ሲነግረኝ በረንዳ ላይ ቆሜ ግቢ ውስጥ ያለውን የሸውሸዌ ዛፍ እየተመለከትኩ ነበር፡፡" ብለን ከመጻፍ ይልቅ

2. "አባቴ አያቴ እሞተች እንደሆነ ሲነግረኝ ግቢ ውስጥ ያለው የሸውሸዌ ዛፍ ቅጠሎች ወዲ ወዲያ ሲንቀሳቀሱ በመሃል በስሱ እያመለጠ የሚገቡትን ብርማ የብርሃን ጨረሮች እየተመለከትኩ ነበር። ብርማዎቹ ቅጠሎች የአያቴ የጸጉር ዘለላዎች የሆኑ አይነት ስሜት ተሰማኝ። በንፋሱ ውስጥም ፍቅር የሚታለበውን የአያቴን ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ።" ብለን ብንጽፍ የተሻለ ነው።

በጽህፈት ዋናው አስቸጋሪው ነገር የገለጻ ጥበብን ፍጹም ማድረግ ነው። ይህ ምስልን፣ገጸባህሪን፣ስሜትን፣ቦታ(ስፍራ) በጽሁፍ ውስጥ ህይወት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው። ገለጻውንም ሆነ ምናባዊ ቋንቋን ለማዳበር አምስቱን የስሜት ህዋሳት መጠቀም ጠቃሚ ነው። በዙሪያችን ያለውን አለም የምንረዳው አምስቱን የስሜት ህዋሳቻችንን በመጠቀም ነው። የምንጠቀምባቸው ሆን ብለን ሳይሆን ወደ እኛ የሚመጡት ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ነው።

**ለምሳሌ፡-**አንድ ሰው አንድን ነገር እንድናሸት ሲጠይቀን አፍንጫችንን እንዴት መጠቀም እንዳለብን እናውቃለን። የሆነ ነገር እንድንዳስስ ሲነገረን ዳሰን መግለጽ እንችላለን። ነገር ግን የስሜት ህዋሳቶቻችንን በእውናዊው ዓለም ለመጠቀም የቱንም ያህል ቀላል ቢሆን አንዳንድ ጊዜ ገጸባህርያቶቻችንን በታሪካችን ውስጥ የስሜት ህዋሳቶቻቸውን ተጠቅመን ማሳየት ይከብደናል።

በአምስቱ የስሜት ህዋሳችን መጻፍ ቀላል ስራ አይደለም ግን ለሚችሉበት ደራስያን የአንባቢዎችን ቀልብ የሚስቡ የበለጸጉ አለሞችን መፍጠሪያ መንገድ ነው። ምንም እንኳን በስሜት ህዋሳት መጻፍ በተሸለ ለታሪካችንም ሆነ ለገጸባህርቶቻችን ህይወት ቢያላብስም ከረጃጅም ገለጻዎች አጫጭሮች ይመረጣሉ።

በጽሁፎቻችን ውስጥ ስሜት ህዋሳትን መጠቀም አንባቢዎችን ከገጸባህርያቱ ጋር እንዲሆኑ ያደርጋል።የታሪኩ አካል እንዲሆኑ እንዲሰማቸው ያደርጋል። ገለጻችን ለገጸባህርያቱ እስትንፋስ ሲለግስ እያንዳንዷ ጥልቅ ዝርዝር ፊት ለፊታቸው ትመጣለች።

## 3.1 በእይታ መጻፍ

ብዙ ጊዜ በጽሁፍ ውስጥ የምንጠቀምበት የስሜት ህዋስ የማየት ነው። የፈጠራ ድርሰት ሰዎች ምልከታ ማድረግ አለባቸው። ትኩረታችንን የያዘ ምስል ፈልገን መግለጽ ያስፈልጋል። አይናቸውን መክፈት ምስሎችን መመልከት፣ነገር ግን ሁል ጊዜ ሌሎች ከሚያዩት በላይ መመልከት አለባቸው።

ከአረንጓዴ ሳር፣ ከሰማያዊ ሰማይ ርቀው ጥልቅ ከለሮችን፣ ቅርጾችን፣መጠኖችን መመላከት አለባቸው፤አዳዲስ ነገሮችን ለማሳየት፡፡

ሰማዩን በቀላሉ ጨለማ ነው ብሎ ከመግለጽ ይልቅ እንደዛ እንዲሆን ያደረጉትን ምክንያቶች ቢመለከቱ ጥሩ ነው፡፡ እይታ በቀላሉ ብዙ ነገሮችን የምንገልጽበት ነው ስለዚህ ክሊሼ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን፡፡ በእይታ ስንጽፍ የምስሉን ጥቅም ዌም ፍቺ መግለጽ አያስፈልግም፡፡ ዝርዝር ሁኔታዎች ፍቺውን እንዲጠቁሙ መፍቀድ ያስፈልጋል፡፡

**ምሳሌ**

ዝላይ ስትጫወት እየዞረ የሚመጣውን ገመድ አይኖቿ እየተቁለጨለጩ ስትጠብቅ፣ከንፈሮቿ ሸሽተው የተከረከሙ የጥርሶቿ ጫፎች ብቅ ሲሉ፣ክልሉ ውስጥ ገብታ ስትዘል፣ነጠላ ጫማዎቿ መሬት የሚገርፈውን የገመድ ዑደት ተከትለው ሲነጥሩ፤ተረከዟ ደም ቋጥሮ አፍረንጅ ስትመስል፣በወፍራሙ የተጎነጎነችው ጸጉሯ ፊቷን፣ትከሻዋን፣ደረቷን ሲገርፍ… ደስታ ያጥለቀለቃት ፊቷ እሳት እንደተለኮሰ የክብሪት አናት ስትቀላ…….. አፌን ከፍቼ አያታለሁ፡፡ (አዳም ረታ፣ ከሰማይ የወረደ ፍርፍር (ላብሮት፣ገጽ 55))

### 3.2. በስሚታ መጻፍ

በአካባቢችን የምንሰማው ነገር ከአለም ጋር ያለንን ግንኙነት ይቀርጻል፡፡ እንደ እይታ ሁል ድምጽም እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ እውናዊ ጽሁፍን ለማቅረብ ታሪካችን በድምጽ ገጽታ እንዲሁም በእይታ ገለጻ መታጀብ አለበት፡፡ ድምጽ የተለያዩ ሁኔታዎችን ሊገልጽ/ ድባቦችን ሊቀርጽ እና የተለያ ስሜታዊ ሁኔታዎችን ሊጠቁም ይችላል፡፡

ለምሳሌ በአስፈሪ ትረካዎች ብዙ ዝምታ አለ፡፡ ብዙ ድርጊት ባለባቸው ትረካዎች ብዙ ድምጽ አለ፤ ፍንዳታዎች ከባድ ድምጾች ይሰማሉ፡፡

ሆኖም ጠንቃቃ ካልሆንን የምንመርጣቸው ድምጾች የታሪካችንን መቼት ወይም ድባብ ሊያበላሹ ይችላሉ፡፡

ለብዙ ጸሃፊዎች ምት ለስልታቸው መሰረታዊ ነው፡፡ ዝርው ስራዎችም ላይ ቢሆንም፡፡ ምንም እንኳን ንባብ በዝምታ የሚከናወን ቢሆንም ምትን በአይናችን እናነባለን፡፡ ደራሲው በቋንቋው የሚፈጥረውን ድምጽ እናደምጣለን፡፡

ጩኸት፣ለስላሳ፣ቁጣ፣ሹክሹክታ፣ ንዴት…ወዘተ. ገላጮች ድምጽን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን እንደ ደራሲ ሁል ጊዜ ግላዊ የሆኑ ገለጻዎችን ለመጠቀም ማሰብ አለብን

**ምሳሌ**

- በድመት ድምጽ ሳሆን በአፍቃሪ ድምጽ ነው እምታወራው፡፡ እያንዳንዷን ሆሄ ጠጋ ብዬ እንዳደን,ምጣት ትገፋፋኛለች፡፡
- እሱ የነጻነት ድምጽ አለው፡፡
- "ቀይ ደማቅ ድምጽ ነበር፡፡ በተከታታይ እና በተደጋጋሚ አቁም፣አቁም፣አቁም የሚል፣ መሄድ እስኪያቅተኝ ድረስ…"

## 3.3. በቀመሳ መጻፍ

ጣእም ለእያንዳንዱ ሰው የተለያየ እና በጽሁፍ ለማስፈርም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሁላችንም ስጋ ምን አይነት ጣእም እንዳለው እናውቃለን እናም ስጋ ስጋ ይላል እንላለን ነገር ግን በዚህ ሃሳብ የተለየ ነገር መግለጽ እንችላለን፡፡

ካሰብንበት በጣዕም አእምሯችን ከጣእም ህዋሳችን ከሚያገኘው መረጃ በላይ ይሄዳል፡፡ ጣእም ገጽታ ነው፣ ሽታ ነው፣ እይታ ነው የሁሉም ስሜት ህዋሳቶቻችን ቅልቅላዊ ሂደት ነው፡፡

ምሳሌ

- በደንብ ያልበሰለው ስጋ ምላሴ ላይ የተቀመጠ እርጥብ እስፖንጅ አይነት ስሜት እንዲሰማኝ አድርጓል፤ከውሃ ይልቅ አፌ ውስጥ ቅባት ሞላ፡፡
- ልክ እንደ ክረምት ገንፎ እራቱ እንድዝናና እና እንድረጋጋ አደረገኝ፡፡

አንዳንድ ጊዜ የቀመሳውን ስሜት ባንገልጽ እንኳን ተግባሩን እንግለጽ፡፡ ከምግብና መጠጥ በላይ ያሉ ነገሮችን እንግለጽ፡፡

ምሳሌ

- በመንገዱ ጫፍ ላይ ታናሽ ወንድሙ የብረቱን ቋሚ ይልሳል፡፡
- የክረምት የመጀመሪያ ቀን ነው፡፡ በረዶ መጣል ጀመረ፡፡ ቀና ብላ የበረዶ ብናኙን ምላሷ ላይ ለማጠራቀም ሞከረች፡፡

## 3.4. በዳሰሳ መጻፍ

ምንም እንኳን ትኩረት ባንሰጠውም ሁል ጊዜ አንድ ነገር እየነካን ነው፡፡ ነገሮችን የምንረዳበት ሁኔታ ከሻካራነተ፣ለስላሳነት ወይም ሙቀት የላቀ ነው፡፡ እንደሌሎቹ የስሜት ህዋሳቶቻችን ሁሉ ግላዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ምሳሌ**

- አጨባበጡ እንደአባቴ ነበር፡፡

ዳሰሳ ህመም የተሞላ ወይም አስደሳች ሊሆን ይችላል፡፡ በበጋ ምሽት የሃር አንሶላ ውስጥ እንደመተኛት አሰደሳች አደርገን አንባቢዎች አንባቢዎች ዲሎቱን ከገጸባህርያቱ ጋር እንዲጋሩ ልናደርግ እንችላለን፡፡ ወይም አፍንጫን እንደመመታት አሳማሚ ልናደርገው አንባቢ እንዲዘሀንነው ልናደርግ እንችላለን፡፡

አንዳንድ ጊዜ ዳሰሳን ገጸባህርያትን ብቻ ለመግለጽ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡

**ምሳሌ**

- ዘይት የጠገበ መጥበሻ
- የተሰነጣጠቀ ከንፈር
- ቀዝቃዛ እጅ

የዳሰሳ ስሜት ቅጽበታዊ ሲሆን ከሌሎቹ የስሜት ህዋሳት በተለየ የሰውነት ንክኪን ይፈልጋል፡፡ ከምንነካው ነገር ውስጥ ለየት ያለ ስሜት የፈጠረብንን ለይተን ማመልከት አለብን፡፡ ከመቼት ጋር በተያያዘ ዳሰሳን ጠንካራ በሆነ ሁኔታ ልንገለገልበት  ይገባል፡፡ ለአንባቢዎች ቅርብ መሆን አለበት ፡፡ የገጸብህርያቱን ስሜት መጋራት አለባቸው፡፡  የውስጥ ወይስ የውጭ መቼት ነው ገጸባህርያቱ ሞቋቸዋል ወይስ በርዷቸዋል፡፡

**ከታች የቀረቡት ሙከራዎች ትምህረት በሚጀመርበት ወቅት የምታቀርቧቸው ናቸው፡፡ ትምህርት በተጀመረ እለት የማያቀርብ ተማሪ ለተግባራቱ የተሰጠውን ውጤት ያጣል፡፡**

## ሙከራ 1. ባለታሪክ መቅረጽ

ይህን ሙከራ ከታች በተቀመጠላችሁ ደረጃ መሰረት ሰርታችሁ በወረቀት ለመምህራችሁ በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ የምታስረክቡ ይሆናል፡፡

1. ለጽህፈት ባዘጋጃችሁት ወረቀት ላይ በግራ ጥግ ጎን የሰው ፊት ሳሉ
2. የሳላችሁትን ሰው አካላዊ መልክ ሚገልጹ አምስት ነገሮች ዘርዝሩ
3. የሳላችሁትን ሰው ባህሪ የተመለከቱ አምስት ነገሮች ዘርዝሩ
4. የሳላችሁትን ሰው ሚወደውን ሶስት ነገሮች ጻፉ
5. ከማን ጋር ይኖራል
6. የት ይኖራል/መቼት

   - እናንተ ያላችሁበትን አንድ ክፍል ከላይ በቀረጻችሁት ገጸባህሪ እይታ ግለጹ፡፡ ገጸባህሪው መጀመሪያ የሚያየው ነገር ምንድን ነው? ከሚያየው ነገር ያልተለመደ ነው ብሎ የሚያስበው ምንድን ነው? ክፍሉ ውስጥ የወደደው ነገር ምንድን ነው? ክፍሉ ውስጥ የጠላው ነገር ምንድን ነው?
   - ክፍሉ ውስጥ የሚታዩትን ነገሮች ከመግለጽ አልፋችሁ የሳላችሁት ሰው ስለሚያየው ነገር ያለውን አመለካከት ለመግለጽ ሞክሩ፡፡

- ✓ እነዚህን ነገሮች ከዘረዘራችሁ በኋላ የመግቢያ አረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

  ምሳሌ፡- ጨለማ እና ነጎድጓዳማ ምሽት ነበር፡፡
- ✓ የመግቢያ አረፍተ ነገሩን ከጻፋችሁ በኋላ ሰለሳላችሁት ሰው የሚገባበት አንድ አጋጣሚ በምናባችሁ አስቡለት፡፡
- ✓ ይህንን መሰረት አድርጋችሁ አንድ ሙሉ ታሪክ ጻፉ፡፡

## ሙከራ 2. ምናብን ማጎልበት

**ሀ.** ሄዳችሁ የማታውቁበትን ቦታ ምረጡ (አጠገባችሁ ካርታ ካለ በነሲብ አንድ ቦታ ላይ ጣታችሁን ጠቁሙና ምረጡ)፡፡ በቻላችሁት አቅም ስለመረጣችሁት ቦታ በተለያዩ መንገዶች ለማወቅ ሞክሩ (አንብቡ፣ ጠይቁ፣ ምርምር አድርጉ)፡፡ በተቻላችሁ አቅም ዝርዝር ነገሮችን በማካተት የምታውቁት ቦታ ይመስል ግለጹት፡፡ ለምሳሌ ቦታው ምን መአዛ ይኖረዋል? ምን አይነት ሰዎች አካባቢው ታያላችሁ? የአየር ንብረቱ ምን ይመስላል፡፡ የተሟላ የመቼት ገለጻ ጻፉ፡፡

**ለ.** በአንድ ትልቅ ሳጥን ፊት ለፊት አንድ አጭር ቀጭን ሰውዬ ቆሟል፡፡ ትልልቅ አይኖቹ ከጉድጓዳቸው ተጎልጉለው ወጥተው የሚወድቁ ይመስላሉ፡፡ አፉ በምራቅ ተሞልቷል፡፡ እያሰበ ነው፣ ይህ የኔ ነው! ከእንግዲህ አይርበኝም፤ ቀጭን ደካማ አልሆንም፡፡

አንድ ግዙፍ ሴት ድንገት ከተፍ አለች፡፡ ትልቁ ሳጥን ባዶ እንደሆነ ሁሉ ብድግ አድርጋው በንፋስ ፍጥነት ሮጠች፡፡ ደቃቃው ሰውዬ ምንም ከማለቱ በፊት ሁለት ፖሊሶች ከኋለው እየሮጡ መጡና አንድ ትልቅ ሳጥን አይተሃል ብለው ጠየቁት፡፡

ሰውየው ወደ ፖሊሶቹ ተመለከተ እና ፊቱን አዞረ፡፡ ሴትየዋ እና ሳጥኑ ግን የሉም፡፡

1. ታሪኩ የት የተከናወነ ይመስላችኋል?
2. ሳጥኑ ውስጥ ምን ያለ ይመስላችኋል?
3. ፖሊሶቹ ለምን በሳጥኑ ላይ ፍላጎት ያደረባቸው ይመስላችኋል?
4. በሳጥኑ እና በሴትየዋ ላይ ምን የደረሰ ይመስላችኋል?

- ከላይ የመለሳችኋቸውን መልሶች መሰረት አድርጋችሁ ታሪኩን ጨርሱት፡፡
- ሙሉ ታሪኩ የሚታረም ይሆናል፡፡

## 5. ኢ-ልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰቶች

እነዚህን በጥሩ ሁኔታ የተነገሩ እውነተኛ ታሪኮች ናቸው፡፡ ስነጽሁፋዊ፣ ጥበባዊ፣ ምናባዊ በሆነ መንገድ የቀረቡ እውናዊ ገጠመኞችን ይመለከታል፡፡ የተለያዩ ጣእሞች፣ሃሳቦች እና ቴክኒኮች ቅንብር ናቸው፡፡

እውናዊ እና ተጨባጭ ነገሮችን ስነጽሁፋዊ ጥበቦችን በመጠቀም ማቅረብን ይመለከታል፡፡ መቼት፣ ድምጸት፣ ገጸባህሪ አሳሳል ሁሉ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ይህ ከመደበኛ ኢ-ልቦለዳዊ ጽሁፎች የተለየ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

ፈጠራ የሚለው ቃል ስነጽሁፋዊ ጥበቦችን መጠቀምን ያመለክታል፡፡ ልቦለድ ጸሃፊዎች እና ገጣሚዎች የሚጠቀሟቸውን የተለያዩ ቴክኒኮችን መጠቀምን ይመለከታል፡፡ እውናው፣ተጨባጭ እና ሰዋዊ ጉዳዮች እና ሁነቶች በዝርው፣ በሚስብ እና ድራማዊ በሆነ መንገድ ይቀርብበታል፡፡

ፈጠራ መባሉን የሚቃወሙ አሉ፡፡ ምክንያቱም ፈጠራ የማጋነን ባህሪ አለው ይህ ትክክል አይደለም ይላሉ ነገር ግን የፈጠራ ድርሰት በተመሳሳይ መልኩም ሃቀኛ፣ ቀጥተኛ እና ድንቅ

ሊሆን ይችላል። በዚህ አውድ ፈጠራ ማለት የሌለውን መፍጠር፣ መግለጽ ወይም ሪፖረት ማድረግ አይደለም። ጸሃፊው የመዋሸት ፍቃድ አለው ማለት አይደለም።

ኢ-ልቦለድ የፈጠራ ድርሰት

- ትክክለኛ እና በጣም የተጠና መረጃ መያዝ አለበት
- የአንባቢውን ፍላጎት እና ስሜት መያዝ አለበት

## 4.1. ወግ

ከጸሃፊው አተያይ አኳያ የሚጻፍ እና አንድን ጉዳይ የሚያብራራ፣ የሚገልጽ ነው። "ከጸሐፊው አተያይ አኳያ የሚጻፍ እና አንድን ጉዳይ አንስቶ የሚያብራራ፣ አጠር ያለ ኢልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰት ነው።

ወግ ብዙውን ጊዜ የሚቀርበው አንባቢን እያዋዙ፣ እያዝናኑ ገመመኘን፣ ሃሳብን ለማስተላለፍ ነው። ስነጽሁፋዊ ጥበቦችን ጠጠቅሞ ጸሃፊው የአንባቢዎችን ስሜት ለመያዝ ይሞክራል።

**የወግ ባህርያት**

**እውነተኛነት**

ወግ ፈጠራ ሳይሆን ኢ-ልቦለዳዊ ስራ ነው። በመሆኑም የወግ ጸሃፊው በአካባቢው የታዘባቸውን፣በራሱ ደረሰውን አልያም ከሌሎች የሰማቸውን ጉዳዮች ማተንጠኛው አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል።የወግ ደራሲ አንዳንዴ ፈጠራ ቢያክልም እንደሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች ምናባዊ ጉዳዮች በዙበት አይደለም።

**ብሩህነት**

ወግ ውስጠ የሚነሱ ጉዳዮች የተብራሩ መሆን ይገባቸዋል። ወግ ብሩህ ሆኖ ካልቀረበ አንባቢን ሊስብ አይችልም። ለዚህም ወግ ጸሃፊውየተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የተነሳበትን ነጥብ ያብራራል። ደራሲው የተነሳበትን ጉዳይ በዝርዝር ለማሳየት ሲል እንደ ትርክት፣አስረጂዎች እና አነጻጻሪ ቀላትን ይጠቀማል።ታዲያ የተነሳበትን ነጥብ የሚያብራራው በቀጥተና ገለጻ ብቻ ሳይሆን አንድን ሃሳብ እያነሳ ሌላን እየጣለ አንድን ግን ዋናውን ክር እየመዘዘ ነው።

**ምጡንነት እና ሚዛናዊነት**

ወግ እጅግም ረዝሞ የተንዛዛ እጅግም አጥሮ ቁንጽል መሆን የለበትም፡፡ ሚዛናዊ ካልሆነም ጸሃፊውን ትዝብት ላይ ይጥላል፡፡ ወገንተኛ ከሆነ ተወዳጅነቱ ይቀንሳል፡፡

**አግባቢነት**

ወግ የጸሃፊው ስሜት ጎልቶ ይንጸባረቅበታል፡፡ እኔ እያለ ከማውራቱ እና ኢመደበኛ ቋንቋ ከመጠቀሙ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

**ምሳሌ**

## ስንተኛው እጣ ነው?

የ1997 ምርጫን ተከትሎ ተነሳ ግርግር ሰሞን የብሄራዊ ሎተሪ ልዩ ቶንቦላ እጣ የሚወጣበት ወቅት ነበር፡፡ እጣው ከመውጣቱ በፊት በሎተሪው ላይ የተመዘገቡት መኪናዎች በአዲስ አበባ አውራ መንገዶች ላይ እየተዘዋወሩ ይተዋወቁ ነበር፡፡

በአንዱ አውራ ጎዳና ላይ ታዲያ የብሄራዊ ሎተሪ የእጣ መኪናዎች በሰልፍ በሚሄዱበት ወቅት "የፌደራል ፖሊስ" የሚል ጽሁፍ ያለበት የጸጥታ ሃይሎችን የጫነ መኪና ከኋላቸው ይከተላቸው ነበር፡፡

ይህን ያስተዋሉ አንድ አዛውንት የፖሊስ መኪናውን በትዝበት አይን እየተመለከቱ፣"ይሄ ደግሞ ስንጠኛው እጣችን ይሆን?" ብለው ሲጠይቁ፣ ከጎናቸው የነበረ ሌላ ሰው፣ "ይሄማ የሁላችንም ድርሻ ነው በማለት ተናግሯል፡፡"

(በሃይሉ ገ/እግዛብሄር 2004 ዓ.ም)

## 4.2. ግለታሪክ እና የሰዎች የህይወት ታሪክ (Autobiography and Biography)

ሁለቱም የአንድን ሰው የህይወት ታሪክ የሚተርኩ ናቸው፡፡ ግለታሪክ የሰዎችን የህይወት ታሪክ የሚመለከት ሲሆን በግለሰቦቹ በራሳቸው ይጻፋል፡፡ የሰዎች የህይወት ታሪክም የሚያትተው ስለሰዎች የህይወት ታሪክ ሲሆን የሚጻፈው ግን በሌላ ሰው ነው፡፡

ሁለቱም በሰዎች የኋላ ታሪክ የተፈተሩ ነገሮችን ያትታሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በተለያ ጉዳች ላይ ትልልቅ ስራ የሰሩ ሰዎች ታሪካቸው ይጻፋል፡፡

**ግለታሪክ**

ስለአንድ ሰው ሙሉ ህይወት የሚያትት ጽሁፍ ነው፡፡ በራሱ በግለሰቡ ይጻፋል፡፡ በአንዳንድ ፖለቲካ መስኮች መሰረታዊ ነው፡፡ በአለም ላይ ያሉ ብዙ የፖለቲካ ሰዎች እና የሃገር መሪዎች ግለታሪካቸውን ይጽፋሉ፡፡ አሁን አሁንም ግለ ታሪክ በተለያየ ዘርፍ ውስጥ ካሉ ታዋቂ ዘርፎችም ይጠበቃል፡፡እነዚህ ሰወች ብዙ ጊዜ ታሪኮቻቸውን እራሳቸው እንደጻፏቸው ቢቀርቡም በድብቅ ጸሃፊዎች (Ghost writers) ያጽፋሉ፡፡

ብዙ ጊዜ ሰዎች ግለታሪኮቻቸውን ሲጽፉ አውንታዊ ገጽታቸው ይጎላል፡፡ ለዚህም ነው ሰዎች ለፈቃዳቸው ታሪካቸው በሌሎች ሰዎች ሲጻፍ ታሪኩ ተቃራኒ የሚሆነው፡፡

**የግለታሪክ ባህርያት**

- የራስ ታሪክ ነው
- በአንደኛ መደብ አንጻር ይቀርባል
- መግለጽ እና መረጃ መስጠት ላይ ያተኩራል
- በስሜት እና በሃሳብ የተሞላ ነው

**ትዝታ (Memoir)**

ይህ የግለታሪክ አይነት ቢሆንም እንደ ግለታሪክ ሙሉ የሰው የህይወት ታሪክ አይቀርብበትም፡፡ ጸሃፊው ካለፈበት ህይወት የተወሰነውን ክፍል ብቻ መርጦ የሚያቀርብበት ነው፡፡

**የሰዎች የህይወት ታሪክ**

ይህ በራሳቸው በታሪኩ ባለቤቶች ሳይሆን በሌሎች ሰዎች የሚጻፍ የህይወት ታሪክ ነው፡፡ የሰዎችን ታሪክ ከውልደት ጀምሮ በምሉእነት ያቀርባል፡፡ የሰዎችን ግለሰባዊ ጉዳዮች ያቀርባል የማንነታቸውን ከፍታ እና ዝቅታ ይዳስሳል፡፡

በሌላ ሰው ቃላት የአንድን ሰው ታሪክ እንደጋና መፍጠርን ይመለከታል፡፡ ሰውየውን የተመለከቱ. እውነታዎች ጸሃፊ ያቀርባል፡፡ጸሃፊው በብዙ ጊዜያት ከተለያዩ ምንጮች የሰበሰባቸውን መረጃዎች መሰረት አድርጎ ይጽፋል፡፡

የታሪኩን ባለቤት እና በዙሪያው ያሉ ሰዎችን ቃለመጠይቅ ሊያደርግላቸው ይችላል፡፡ በሰውየው ዙሪያ በተለያዩ የህትመት እንዲሁም የብሮድ ካስት ሚዲያዎች የውጡ መረጃዎችን ስብስቦ መጠቀም ይገባል፡፡ ይህ ግለኝነት እና ጠባብነት እንዳይፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

**የሰዎች የህይወት ታሪክ ባህርያት**

- የሰዎች ታሪክ ነው
- በሶስተኛ መደብ አንጻር ይቀርባል
- መረጃ ይሰጣል
- በጸሃፊው የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት ያደርጋል
- በባለቤቱ ፍቃድም ያለፍቃድም ሊጻፍ ይችላል

## 6. ልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰት

ከምናብ የተቀዳ ማንኛውም ጽሁፍ ልቦለድ ይባላል፡፡ ልቦለድን መጻፍ አለምን መፍጠር ነው፡፡ ስለዚህም አንባቢዎች ጽሁፉ ሙሉ ለሙሉ ለእውኑ አለም ታማኝ እንዲሆንና እውነተኛ ገጸባህርትን እንዲሁም ገለጻን እንዲካትት አይጠብቁም፡፡ ከዚህ ይልቅ የልቦለድ አውድ ሙሉ ለሙሉ ከእውኑ አለም ጋር የተጣበቀ እና ለተለያዩ አረዳዶችና ትንታኔዎች ክፍት እንደሆነ መግባባት አለ፡፡

በልቦለድ ገጸባህርያት እና ሁነቶች በራሳቸው አውድ ሊቀረጹ እና ከምናውቀው ሁለንተና ሙሉ ለሙሉ ሊነጠሉ ይችላሉ፡፡ ነጻ የሆነ ልቦለዳዊ ሁለንተና ሊኖራቸው ይችላል፡፡

ከልቦለዳዊ የፈጠራ ድርሰቶች ውስጥ ረጅም ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ ፣ ተውኔት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

### 6.1. አጭር ልቦለድ

ስነጽሁፍ ምንድነው? ወይም ደግሞ ረጅም ልቦለድ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ሁሉንም የጥበቡን ታዳሚዎች የሚያስማማ መልስ እስከዛሬ አልተገኘም፡፡ ከዚህ በመነሳት በአጠቃላይ ስነጽሁፍ፣ በተናጥል ደግሞ አንድን የስነጽሁፍ ዘር ወስዶ ምንነቱን አሟልቶ መግለጽ አዳጋች ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለአዳጋችነቱ እንደምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ነጥቦች አያሌ ናቸው፡፡ የስነጽሁፍ ዘሩ በይዘት፣ በቅርጽ፣በቴክኒክ፣ በስልት ወዘተ አለመወሰን፣ በያኙ እንደሚከተለው የኪነጥበብ ፈለግ ብያኔው የሚወሰን መሆን፣ ወዘተ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ከዚህ አንጻር አጭር ልቦለድም ከላይ የተገለጹትን ባህሪያት የሚጋራ አንድ የስነጽሁፍ ዘር በመሆኑ ምንነቱን አሟልቶ የሚገልጽ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እስከዛሬ አልተገኘም፡፡ የተደረጉ አያሌ ሙከራዎች አሉ፡፡ ሙከራዎቹ ሁሉንም የጥበቡን ሰዎች በአንድነት የሚያግባቡ ግን አይደሉም፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ አጭር ልቦለድ (short story) የሚለውን ስያሜ የተጠቀመው አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ብራደር ማቴዎስ (Brander Matthews) ሲሆን ይህም በ1884 እ.ኤ.አ ነው፡፡ከዛን ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ዘውጉን ከተለያየ የትኩረት አቅጣጫ በመመልከት "አጭር ልቦለድ" ስለሚወክለው ጽንሰ ሀሳብ ማብራሪያን ሰጥተዋል፡፡ምሁራኑ አጭር ልቦለድን ለመበየን ሲሞክሩ ታሳቢ ካደረጓቸው የትኩረት ነጥቦች መካከል ተከታዮቹን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሰጥተዋል፡፡ምሁራኑ አጭር ልቦለድን ለመበየን ሲሞክሩ ታሳቢ ካደረጓቸው የትኩረት ነጥቦች መካከል ተከታዮቹን መጥቀስ ይቻላል፡፡

- አንዳንዶች አጭር ልቦለድ በሚነበብበት ጊዜ የሚወስደውን የጊዜ መጠን ታሳቢ በማድረግ
- አንዳንዶች የአጭር ልቦለድ የቃላት ብዛትን በማገናዘብ
- ሌሎች የአጭር ልቦለድን ከሌሎች ተቀራራቢ የስነፅሁፍ ዘርፎች ጋር በማነፃፀር /ከተረት፣ ስኬች፣ ረጅም ልቦለድ/
- አንዳንዶች ደግሞ የአጭር ልቦለድ ባህሪያት ላይ በማተኮር የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ብያኔዎቹ የትኩረት ነጥባቸው ያደረጓቸውን ጉዳዮች ስናስተውል የምንገነዘበው አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ለንባብ የሚወስደው ጊዜ ከአጭር ልቦለድ እጥረት ወይም ርዝመት ጋር መገናዘቡን፤ የአጭር ልቦለድ የቃላት ብዛት አሁንም ከአጭር ልቦለድ እጥረት እርዝመት ጋር መዛመዱን፡ ከሌሎች ዘሮች ጋር ማነፃፀራቸው ሌሎች ባህሪያቱ እንዳሉ ሆነው ነገር ግን ማጠርና መርዘሙ በውስጣቸው መያዛቸውን ነው፡፡ በመሆኑም አጭር ልቦለድ እንደ ስሙ **አጭር** መሆኑን ከወዲሁ ሳንገነዘብ አናልፍም፡

የአጭር ልቦለድን ምንነት ለመግለጽ የተደረጉ አንዳንድ ሙከራዎች አጭር ልቦለድን በቃላት ብዛት የሚወስኑ ናቸው፡፡

ሆልማን (1980) "አጭር ልቦለድ በሀተታ የሚቀርብ በ500 ቃላት ከሚጻፈው አጭር አጭር ልቦለድ እስከ 12000 ቃላት ያለውን ረጅም አጭር ልቦለድ ይደርሳል፡፡" ይላል፡፡

በስነጽሁፍ መዝገበቃላቱም አጭር ልቦለድ ከ10000 ቃላት በታች የሚይዝ፣ አንድ ዋነኛ ግብ ለማምጣት የሚዋቀር… አንድነት በዋናነት የሚታይበት አጠር ያለ ትረካ እንደሆነ ሃሪሽ(1972፣343) ያብራራል፡፡

ከኢትዮጵያዊያንም አስፋው ዳምጤ አጭር ልቦለድ ራሱን የቻለና ምሉዕ የሆነ ከ500እስከ 10000 ቃላት በሚደርስ አንድ የተወሰነ ጭብጥ በብቃት አብራርቶ ለአንባቢ የሚያቀርብ የስነጽሁፍ ዘር እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ይህ የአጭር ልቦለድ እጥረት ልኬት  በብዙ ምሁራን አወዛጋቢ እንደሆነ ቆይቶል፡፡ ብራደር ማቴዎስ የአጭር ልቦለድ ከ7000-9000 ቃላትን የሚይዝ እንደሆነ ሲገልጽ ሌሎች ከ7500 ቃላት በታች የሆኑ ቃላትን የሚይዝ ይሉታል፡፡ ከዚህ በታች የቃላት ብዛት ያለው ሌሎች የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን የሚያሟላ ዝርው ትረካ አጭር ልቦለድ አይባልም ወይ? የሚለው አከራካሪ ሆኖ እንዲቆይ አድርጎታል፡፡

በሌላ መልኩ የአጭር ልቦለድ ከ20,000 ቃላት በላይ ባልበለጡ ከ1000 በታች በሆኑ ቃላት የሚጻፉ ናቸው የሚሉም ምሁራን አሉ፡፡ ከአንድ ሺህ ቃላት በታች በሆኑ ቃላት የሚጻፉትንም ‹የአጭር አጭር ልቦለድ› በማለት ይሰይሟቸዋል፡፡

የቃላት ብዛት የአጭር ልቦለድን መጠን ጠቋሚ ሊሆን ቢችልም የስነጽሁፍ ዘሩን ምንነት አሟልቶ አይገልጽም፡፡

ከዚህ ሌላ የአጭር ልቦለድን መጠን በሌላ መንግድ የሚገልጹ ብያኔዎችም ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ዋለስ" አጭር ልቦለድ በግማሽ ሰዓት ሊነበብ የሚችል አጭር የፈጠራ ሥራ ነው፡፡" ዘሪሁን፣1992 ይላል፡፡ እንደዚሁ አጭር ልቦለድ ታሪክ አንባቢን በፍጥነት የሚያረካ፣ የህይወትን ትርጉም በመጠኑ የያዘ ሲሆን እንደሆነ ታደሰ ሊበን ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል "አጭር ልቦለድ የጽሁፉን ፍሬ ነገር ባጭሩ በተቀነባበረና በቀለጠፈ አኳኋን ለአንባቢ ለማስረዳት የሚያስችል የአጻጻፍ ስልት

ነው ሲል አለማየሁ ፈጠነ (1961)" "የስሜት መስታወት" አጫጭር ልቦለድ መግቢያ ላይ አስፍሯል፡፡

የአጭር ልቦለድ ብያኔዎች አጭር ልቦለድን በመጠን ከመግለጽ ባለፈ፣ በሀተታ የሚቀርብ፣ አንድነት ያለው፣ አንድ ዋነኛ ግብ ለማምጣት የሚዋቀር ወዘተ አንድ የስነጽሁፍ ዘር መሆኑን ያመለክታል፡፡

የቃላቱን ብዛት ወደ ጎን በመተውም በሌሎች የዘውጉ ባህሪያት ላይ አትኩረው የተሰጡትን ብያኔዎች ደግሞ እንመልከት፡፡

የአጭር ልቦለድ ሀያሲና ደራሲ የሆነው ኤድጋር አለን ፖ የሰጠው የመጀመሪያ ብያኔ "ለመነበብ ከግማሽ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት የሚወስዱ አጭር ዝርው ትረካ" የሚል ነው፡፡ ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው አጭር ልቦለድን አጭር ሲሆን እጥረቱም ለመነበብ ከግማሽ  እስከ ሁለት ሰዓት የሚረዝም ነው፡፡ ይህ የፈጠራ ስራ  በቅርጹ ዝርው ከመሆኑም በተጨማሪ ‹ትረካ› ነው፡፡ይህ አጭር ልቦለድ የሚዘረዝር የሚተረተር ሁነቶች አንዳሉት ይጠቁማል፡፡

በሌላ በኩል አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ጋር ከ አነጻጸሩ  ብያኔዎች መካከል

"አጭር ልቦለድ የስነ ምግባር /ሞራል/ ክስተት የሚታይበት ነው፡፡"(ፈ.ቃደ፤32)

ይህንን የአጭር ልቦለድ ብያኔ ያስቀመጡ ሀያሲያን ረጅም ልቦለድ በተቃራኒ "የስነ ምግባር/ሞራል እድገት የሚታይበት" መሆኑን ይጠቁሚል፡፡

እዚህ ላይ የምናስተውለው ዩሐንስ ሁለቱም ዘውጐች የሚያነሱት ጉዳይ /ይዘት/ አንድ መሆኑን ነገር ግን የጉዳዩ አቀራረብ ለአንዱ/ለአጭር ልቦለድ/ ፈጣንነት ቁጥብነት ባለው መልኩ መሆኑን /ክስተት/ በሚል ሲገልፀው ለሌላኛው /ለረጅም ልቦለድ/ ደግሞ የሚነሳው ጉደይ ደረጃ በደረጃ በሂደት የሚታይ መሆኑን ማስገንዘቡን ነው፡፡

የአጭር ልቦለድ የስነምግባር ራዕይ የሚታይበት የሚለውን ዮሐንስ ሲያስረዳ "አጭር ልብወለድ ድንገተኛ፣ ፈጣን፣ የለዘበ ጦር የሚወጋ፣ የተባ ሰይፍ የሚቀላ ነው ማለት ነው የሚያቀርበው ራዕይ/ዋነኛ ጉዳይ/ ድንገተኛ፣ ፈጣን፣ እንደ ጦር የሚወጋ፣ እንደ ሰይፍ የሚቀላ ራዕየ ያቀርብልናል ማለት ነው"(ፈ.ቃደ:33) በማለት ይገልፀዋል፡፡

የአጭር ልብወለድ የታመቀ ነው፡፡ በዚህ ባህሪውም ሀያሲያኑ ከግጥም እና ከቅኔ ጋር ያዛምዱታል፡፡ ይህ የታመቀ ነገር ግን ከግጥም በተለየ መልኩ በዝርው የሚቀርብ የፈጠራ ስራ የሚያነሳውን ጉዳይ ከጅምሮ አስተዋውቆ በፍጥነት የሚያስጉዝ ነው፡፡ አጭር ልቦለድ ብዙ ነገሮችን ለማስተናገድ ጊዜ የለውም፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ያማከለውን የዘሪሁን ብያኔ እንመልከት፡፡

“አጭር ልቦለድ ሰብሰብ ያለ ወይም የታመቀ ጠባቃ ትስስር ያለው፤ ፈጣንነት ጎልቶ የሚታይበትና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ አጭር ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው የልቦለድ አይነት ነው”(ዘሪሁን፡229)

እንግዲህ ብራደር ማቴዎስ “አጭር ልቦለድ” በማለት የሰየመው ይህ **የሰነፅሁፍ ዘር በዝርው የሚቀርብ፤ ከሕይወት የተመዛዘነ አንድ ቅንጣት ጉዳይ በፍጥነት ወልዶ በፍጥነት አሳድጎ በፍጥነት የሚቋጭ የልቦለድ አይነት ነው ልንል እንችላለን፡፡**

የአጭር ልቦለድ ባህሪያት

ማንኛውም ስነጽሁፍ በቋንቋ አማካይነት በመቅረቡ፣ የማህበረሰቡን ህይወት ለስነጽሁፉ መነሻ በማድረጉ፣ ልቦለዳዊ በመሆኑና አንዳንድ እዚህ ባልተገለጹ ባህሪያት እንደሚመሳሰል መገመት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል አንድ የስነጽሁፍ ዘር የስነጽሁፍ ዘር ለመባል ከሌሎች ስነጽሁፍ ዘሮች ተለይቶ የሚታወቅበት የራሱ ባህሪያት ሊኖሩት የግድ ነው፡፡ የራሱ የተለየ ባህሪ ከሌለው ከሌሎች መሰሎቹ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት መሆኑን እንጂ ተለይቶ መታወቁን አያመለክትም፡፡ ይህም ማለት ለምሳሌ አጭር ልቦለድ የራሱ መለያ ባህሪያት ከሌሉት ከረጅም ልቦለድ አይለይም ማለት ነው፡፡

## 1.1.1.ነጠላ ውጤት

ከአጭር ልቦለድ ባህሪያት መካከል በዋነኝነት የሚነሳውና ለሌሎቹም ባህሪያቱ መሰረት የሚሆነው “ነጠላ ውጤት” የተባለው ነው፡፡ ነጠላ ውጤት የአጭር ልቦለድ የሚያነሳው ጉደይ “ነጠላ” ወይም “ብቸኛ” መሆን እንዳለበት የሚያመላክት ነው፡፡

ነጠላ ውጤት ሁሉም የአጭር ልቦለድ አካላት ተሳስረው ወደ አንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈስሱበትና ደራሲው በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነጥበባዊ ግብ ነው ይባላል፡፡

ነጠላ ውጤት የአጭር ልቦለድ ደራሲ ይሁነኝ ብሎ በማሰብ በልቦለዱ ቀደም ብሎ የሚወጥነው ግብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉም የአጭር ልቦለድ አባላት በልቦለዱ ይህንን ግብ በሚያሳካ መልኩ ይቀናጃሉ ማለት ነው፡፡

ይህን ሃሣብ ዮሐንስ ሲያስረዳ "የአጭር ልቦለድ ደራሲ ከረጅም ልቦለድ ደራሲ በተቃራኒ ራሱን ይወስናል" ይላል "በሚፅፈው አጭር ልቦለድ ውስጥም መሰንዘር ያለበት አንድ ጭብጥ መትለም ያለበት አንድ ትልም መፍጠርም የለበት ጥቂት ገፀባህሪያትን ብቻ ነው" በማለት ያስረዳል፡፡ /ዮሐንስ፡ 34/

የአጭር ልቦለድ ደራሲ ለመፃፍ ሲነሳ አስቀድሞ ስለሚፅፈው ነገር /ጉዳይ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ማወቅ ብቻም ሳይሆን ጉዳዩን እንዴት ባለ መልክ ጀምሮ በምን መልኩ ማጠቀቅ እንዳለበት ያውቃል፡፡ ለዚህም ማስረጃው በአጭር ልቦለድ ደራሲያን የሚባለው አባባል ነው፡፡ አንዳነዶች መፃፍ የሚጀምሩት ከታሪኩ ጅማሪ ሳይሆን ፍፃሜ ላይ መሆኑን መጠቆማቸው፡፡

ይህንን አንድ ብቸኛ ጉደይ ይዞ የሚነሳው ድርሰት ታዲያ ከዚህ ብቸኛ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት የሌለው አንድም ገለፃ(የገፀባህሪያት ይሆን የመቼት ወይም የሌላ)፤ አንድም ምልልስ፤ አንድም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለው ቃል መሰፈር እንደሌለበት ምሁራኑ ይጠቁማሉ፡፡

በመሆኑም ዮሐንስ እንዳለው የገፀባህሪያት በቁጥር መወሰን አካላዊና ህሊናዊ ገለፃቸው ታሪኩ ላነገበው "አንድ ብቸኛ ጉዳይ" አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆን ይገባዋል፡፡ የግጭቱ መንስኤ፣ የእድገቱ ሰበብ፣ የገፀባህሪያቱ ትንንቅንቅና የሚገቡበት ፍትጊያ እንዲሁም ሽንፈትና ድላቸው ሁሉ ከዚህ ልቦለዱ ካነሳው ብቸኛ ተተኳሪ ጉዳይ ጋር በጥብቁ መቆራኘት ይገባዋል፡፡ ተራኪው የገፀባህሪያቱን መኖሪያ ቦታ እና ጊዜው የእነዚህን ጓዝ ሁሉ ሲገልጽልን አሁንም የልቦለዱን ዋነኛ ጉደይ ታሳቢ አድርጐ መሆን ይኖርበታል፡፡

ይህ ሲሆን የልቦለዱ ርዕስ፣ የቋንቋ አጠቃቀሙ፣ የገፀባህሪያት አቀራረጹና አቀራርቡን ጨምሮ የታሪክ አገነባቡ/አወቃቀሩ/ እና ይህን ሁሉ የቀረበበት ለትረካው የመረጠው የእይታ መንፅሩ/አንፃሩ/ ጭምር "ነጠላ ውጤት" አደራጅ አጕልቶም አሳይ ሆኖ እናገኘዋል፡፡

## 1.1.2.ቁጥብነት

ተራኪው የልቦለዱን ታሪክ በሚነግረን ጊዜ የሚያመጣው አንዳች ነገር /የገፀባህሪ ገለፃ እንበል የታሪክ ቅደም ተከተል ትረካ ወይም መቼት ወይም ደግሞ ማናቸውም የትረካ ስልቶች በመጠቀም የሚያመጣው ግጭት፣ የገፀባህሪ እውቂያ ሁሉ ለታሪኩ ዋና መልዕክት አጋዥ መሆን እንዳለባቸው ይህም ነጠላውጤቱን በተጣደፈ መልኩ ለማቅረብ እንደሚረዳው አይተናል፡፡ ይህ ነጠላ ጉዳይ በፍፁም ጥድፊያ እንዲጓዝ ታዲያ ነጠላ ውጤቱን አጋዥ የሆኑትም ጉዳዮች ሲመጡ በተቻለ መጠን ተቆጥበው /ተመጥነው/ መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡

ለልቦለዱ የታሪክ የአሁን ጊዜ ትናንትን ማምጣት አስፈልጎ ቢሆን ከትናንት የታሪኩ ሁነቶች መሃል አስፈላጊውን ብቻ መወሰኑ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊውንም ቆጥቦ መርጦ መውሰድን የቁጥብነት መርህ ይመለከታል፡፡

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር አለ፡፡ ይኸውም ሶስቱ በተናጠል የቀረቡ የአጭር ልቦለድ ባህሪያት አንዳቸው ከአንዳቸው ፍፁም የሆነ ትስስር እንዳላቸው ነው፡፡ በታሪክ ውስጥ ነጠላ ጉዳዩን የማይመለከት ጉዳይ ማምጣት የታሪኩን ቁጥብነት ያፈልሳል፡፡ የቁጥብነቱ መፍለስ ታሪኩ ፈጥኖ እንዳይጓዝ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በፍፁም ተቆጥቦ በጥድፊያ ሳይጓዝ ግራና ቀኝ ታሪኩን ማስኬድ ከዋናው ነገር ጉዳይ ውጭ ሌሎች ጉዳዮችን ታሪኩ እንዲያግበሰብስ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የአንዱ ባህሪ ስኬት ለሌላው ባህሪ ስኬት ክሽፈቱም ክሽፈት መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡

የአጭር ልቦለድ ቁጥብነት በአጭር ልቦለድ ውስጥ በአጠቃላይ በልቦለዱ አላባዊያንና ዘዴዎች አጠቃቀም ላይ ይገለጻል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሲባል ቁጥብነት ከታሪክ፣ ከግጭት፣ ከሴራ፣ ከገጸባህሪ አሳሳል፣ከመቼት፣ ከትረካ አንጻር፣ ከቋንቋ ወዘተ እና ከሌሎች ዘዴዎችም ማለትም ከንግር፣ ከምልሰት፣ ከገለጻ ወዘተ አንጻር ሊገለጽ ይችላል፡፡ በአጭር ልቦለድ ውስጥ በእነዚህ በአላባዊያንና በዘዴዎች ላይ ያለውን ቁጥብነት ለማሳየት እያንዳንዱን መተንተን ተገቢ ነው፡፡

ውድ ተማሪዬ! የአጭር ልቦለድ ታሪክ ነጠላ ነው፡፡ እንደ ረጅም ልቦለድ ታሪክ አጭር ልቦለድ ታሪክ ተቀጽላና ተጓዳኝ ታሪኮች ሊያዝ አይችልም፡፡ አጭር ልቦለድ ተቀጽላና ተጓዳኝ ታሪክ በያዘ ቁጥር ታሪኩ እየሰፋና እየተለጠጠ ስለሚሄድ ሥራው ቅርጹንም ይዘቱንም ያጣል፡፡ የአጭር ልቦለድ ታሪክ ነጠላም ቢሆን ከልደት እስከሞት፣ ከጅምር እስከፍጻሜ ዓይነት ረጅም ታሪኮችን ሊያስተናግድ አይችልም፡፡ በመሆኑም አንድ አጭር ልቦለድ ታሪክ ቁጥብነትን ይጠብቅ ዘንድ የሚይዘው ታሪክ ነጠላ ነው፡፡ ነጠላም ሆኖ ታሪኩ በአንዲት ቅጽበታዊ የህይወት ገጽታና ገጠመኝ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ከዚያም በላይ አጭር ልቦለድ ያችን ገጠመኝ ከጅምር እስከ ፍጻሜ አይገልጽም፡፡ ከግቡ አንጻር ጠቃሚ ነው ብሎ ከሚያስበው ሁነት ጀምሮ ታሪኩን የግዴታ አንጠፍጥፎ ሳይጨርስ ተገቢ ነው ብሎ በሚያስበው የታሪክ ሁነት ላይ ልቦለዱ ይገታል፡፡

የአጭር ልቦለድ ታሪክ ነጠላ በመሆኑ ሴራውም ነጠላ ነው፡፡እንደ ታሪኩ ሁሉ ተጓዳኝ ሴራ የለውም፡፡ ሴራና ታሪክ የተገናኙ ናቸው፡፡ ሴራው ተጓዳኝ ከሆነ ታሪኩም ተጓዳኝ ይሆናል፡፡ ተጓዳኝ ሴራ አጭር ልቦለድን ቁጥብነት ያሳጠዋል፡፡ ከቅርጹ ውጭም ያወጠዋል፡፡ ስለሆነም በሴራው ነጠላነት አጭር ልቦለድ ቁጥብነትን ይቀዳጃል ማለት ነው፡፡

በአጭር ልቦለድ በገጸባህሪያት አንጻርም ቁጥብነት ይገለጻል፡፡ የአጭር ልቦለድ ገጸባህሪያት በቁጥር ጥቂት ናቸው፡፡ ለምሳሌ በተመስገን ገብሬ የጉለሌው ሰካራም ገጸባህሪ በዋናነት ተበጀ ነው፡፡ ሌላ በታሪኩ ያላት ተሳትፎ አነስተኛ ቢሆንም ሠራተኛው በሁለተኛነት ልትጠቀስ ትችላለች፡፡

ውድ ተማሪዬ! በማንኛውም ልቦለድ ከሚገለጹት ጉዳዮች አንዱ በገጸባህሪያት መካከል ያለን መስተጋብር ነው፡፡ በአጭር ልቦለድ የገጸባህሪ ቁጥር ጥቂት መሆን በገጸባህሪያቱ መካከል ያለውን መስተጋብር ውስን ያደርገዋል፡፡ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ገጸባህሪያትን መመጠን ብቻ ቁጥብነትን አያስጠብቅም፡፡ የሚቀርቡ ገጸባህሪያት ታሪካቸውም ከመለጠጥ መጠበቅ አለበት፡፡ በአጭር ልቦለድ ገጸባህሪያቱ የተመጠኑ ከመሆን ባሻገር ከህይወት ገጠመኛቸው በአንዲት ቅንጣት ላይ ብቻ መተኮር አለበት፡፡ ገጸባህሪያትን አስፋፍተን ከተለያየ አቅጣጫ በአጭር ልቦለድ መቅረጽ ልቦለዱን ቁጥብነት የሚያሳጣው እንደሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡ ለዚህም ሲባል ከአለአስፈላጊ የገጸባህሪ ገለጻ መቆጠብ ተገቢ ነው፡፡ ለልቦለዱ ታሪክ የሚፈጥረው አንዳች ፋይዳ ከለለ የገጸባህሪም ሆነ የአካባቢ ወዘተ ገለጻ በአጭር ልቦለድ ቁጥብነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራቸዋል፡፡

የአጭር ልቦለድ ቁጥብነት ከመቼቱም አንጻር ይገለጻል፡፡ አጭር ልቦለድ መቼቱ ጠባብ ነው፡፡ አጭር ልቦለድ የሚያካልለው ቦታም ሆነ ጊዜ ጠባብ ነው፡፡ መቼቱ በአጭር ልቦለድ ጠባብ ብቻ

መሆን ሳይሆን ከአለአስፈላጊ የመቼት ገለጻም መቆጠብ ያስፈልጋል፡፡ ማናቸውም ድርጊት ወይም ታሪክ የሚፈጸመው በጊዜና በስፍራ ክልለ ውስጥ መሆኑ ቢታወቅም በልቦለድ ውስጥ መቼትን ለመቼት ሲባል ብቻ መጠቀም አለአስፈላጊ ይሆናል፡፡ ቁጥብነትንም በአጭር ልቦለድ ውስጥ ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ለዚህም ሲባል በአጭር ልቦለድ ውስጥ ብዙውን ጊዜ መቼትን ከድርጊት ወይም ከገጸባህሪ አሳሳል ጋር አዋህዶ መግለጽ የበለጠ ቁጥብ እንዲሆን ይረዳል፡፡ ይህ የሚሆነው መቼቱን በገሃድ መግለጹ ለልቦለዱ ቅርጽም ሆነ ይዘት ፋይዳ እስከለለው ድረስ ነው፡፡ ውድ ተማሪዬ! በመቼት አጠቃቀም ለምሳሌ የስብሃት ገብረእግዚአብሄር እትዬ አልታዬን ብንመለከት በዚያች ታሪኩ በጀመረበት በእትዬ አልታዬ መጠጥ ቤት ነው የሚያበቃው፡፡ ይህ በስፈራው የመቼቱን ጠባብነት ያመለክታል፡፡

ውድ ተማሪዬ! በአጭር ልቦለድ ቁጥብነት ከሚታይባቸው ገጽታዎች ሌላኛው የትረካ አንጻር ነው፡፡ በመሠረቱ አንጻር በልቦለድ ውስጥ የአተራረክ አቅጣጫ ነው፡፡ ታሪኩ የሚቀርብበት ፡፡ ረጅም ልቦለድ በታሪኩ ውስጥ የአንጻር ለውጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በአጭር ልቦለድ ታሪክ ግን በአንድ ደራሲው በመረጠው አንጻር ነው የሚቀርብ፡፡ ታሪክን በተለያየ አንጻር ማቅረብ አጭር ልቦለድን ሌላው ቢቀር ይለጥጠዋል፡፡ ለምሳሌ **ደብዳቤው** አጭር ልቦለድ የሚተርከው አበይት ገጸባህሪው መዳቡ ዳዲ«እኔ» እያለ ነው፡፡ በዚህ አተራረኩ አጭር ልቦለዱ የቀረበው በአንደኛ መደብ አንጻር ነው፡፡ ታሪኩ ተጀምሮ እስከሚያልቅ የተጠቀመው ይህንኑ አንጻር ነው፡፡ የአንጻር ለውጥ አልተደረገም፡፡ አጭር ልቦለድ በመሆኑ የአንጻር ለውጥ መደረግም የለበትም፡፡ በጀመረው አንጻር መጨረሱ ተገቢ መሆኖን ካመለከትን ወደ በግጭት ላይ ቁጥብነትን እንመልከት፡፡

የአጭር ልቦለድ ግጭት ቁጥብነትን ለአጭር ልቦለዱ ያስገኝ ዘንድ ለአጭር ልቦለድ ቅርጽ የሚበጅ መሆን አለበት፡፡ አንደኛ ነገር ሰፊ መሆን የለበትም፡፡ግጥቱ ተጣማሪና የተለያየ መሆንም የለበትም፡፡ ከግጥቱ መንስኤ ነገር እስከ እስከ ልቀቱ ያለው ሂደት መቅረብ ያለበት በዝርዝር ሳይሆን በስልትና በፍጥነት ነው፡፡ ለዚህም ዝርዝር ነገር ውስጥ ሳይገባ ግጭቱ ወዲያው ሲፈጠር ፣ሲወሳሰብና አድጎ ጡዘት ሲደርስ፣ ከዚያም ወዲያው ችግሩ እየተፈታ ሄዶ መፍትሄ ሲያገኝ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ልንመለከት ይገባል፡፡

በአጭር ልቦለድ ውስጥ አንድም ቃል ቢሆን አስፈላጊነቱ ታይቶ ነው የምንጠቀመው፡፡ አለአስፈላጊ ገለጻ፣ አለአስፈላጊ ሀተታ፣ አለአስፈላጊ ምልልስ፣ ወዘተ በአጭር ልቦለድ ቦታ የላቸውም፡፡ ይህም በመሆኑ በአጭር ልቦለድ ሁሉም ነገር የሚቀናጀው ቁጥብነትን መሠረት በማድረግ ነው ማለት

ይቻላል፡፡ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ቁጥብ እንዲሆኑ የሚጠበቀው በልቦለድ አላባዊያን ብቻ ሳይሆን በልቦለድ ዘዴዎች አቀነጃጀትም ጭምር ነው፡፡ ንግር፣ ምልሰት፣ ገለጻ፣ ወዘተ በተንዛዛ ሁኔታ መቅረባቸው የማይደገፈው አጭር ልቦለድን ቁጥብነት የሚያሳጡ በመሆናቸው ነው፡፡

### 1.1.3. ጥድፊያ

አጭር ልቦለድ አንድ ብቸኛ ጉዳይ ይዞ የሚፃፍ ዝርው የፈጠራ ትረካ መሆኑን አይተናል፡፡ ይህ አንድ ብቸኛ ጉዳይን ይዞ የሚቀርበው ትረካ የያዘውን ብቸኛ ጉዳይ ሲያቀርብ በአቀራረቡ ፈጣንነት ያለው፣ ሂደትን የሚከተል መሆኑን የሚመለከተውን ባህሪ “ጥድፊያ” እንለዋለን፡፡

በልቦለዱ የመጀመሪያ ክፍል የመጀመሪያ አንቀጽ ላይ ተወልዶ ያየነው ታሪክ ብዙም ሳይቆም ምናልባትም በዛው  አንቀጽ ወይም በተከታዩ ታሪኩ አድጐ ሲራመድ እናየዋለን፡፡  ይህ ጥድፊያ የአጭር ልቦለድ አጭር በመሆኑና ከሚያነሳው አንድ ብቸኛ ጉደይ በቀር ሌሎች ዝርዝሮችን የማይጨምር ከመሆኑ የሚመነጭ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሌሎችን አላባ ያየን እንደሆነ ለምሳሌ ግጭትን ተራኪው የግጭቱን መንስዔ ነግሮን አፍታም ሳይቆይ እድገቱን እናስተውላለን፡፡  በአንድ ብቸኛ ግጭት የሚገነባ ስለሆነም ብቸኛው ታሪክ ያሳደገው ግጭት እጡዘት ለማድረስ አሁንም ጊዜ አይፈጅበት፡፡  በመሆኑም አንባቢ በሚያነባቸው ተከታታይ ዓ.ነገሮች ሀረጋት ወይም ቃላት ሁሉ የታሪኩን እድገት እያስተዋለ ሳይሆን በታሪኩ እድገትና በሚከናወነው ሁነት ሁሉ እየተደመመ ይሄዳል፡፡ በድንገትም ፍፃሜውን ያስተውላል፡፡

ይህን የአጭር ልቦለድ ጥድፊያ ዮሐንስ ከገደል ላይ ተወርውሮ ወይንም ተፈንቅሎ ከሚንከባለለሁ ደንጊያ ፍጥነት ጋር ያዛምዱታል፡፡  ግን ደግሞ በዚህ ጥድፊያ ውስጥ አጭር ልቦለድ መለዘብ “ማደብ” ማድፈጥ እንበለው እንዳለው ይገልፃል፡፡ “አጭር ልቦለድ እንደ ቋያ እሳት፣ ፍሪዳ እንደሚሰብር አንበሳ፣ እስትፋሱ እየተቁረጠ፣ መሬቱን እየፎገረ፣ ድሩን በቀኑን እየገለጠ ከፈላው እንደሚወጣ ጉሽ፣ ከገደል ላይ ተወርውሮ ወይም ተፈንቅሎ እንደሚከባለለው ደንጊያ ፈጣን፣ ድንገተኛ፣ ለዝቦ፣ አድቦ የተጣደፈ ነው፡፡ (ፈቃደ፡34)

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከልቦለዱ ተተኮሪ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት የሌላቸው ጉዳዮችን የሚያስተናግድ ሲሆን የአጭር ልቦለዱ ቁጥብነት ይፋለሳል፡፡ለምሳሌ የድህነትን አስከፊነት ዋና ጉዳዩ አድርጎ የተነሳ አንድ አጭር ልቦለድ የገጸባህሪያት ገለጻው (አካላዊም ሆነ ሕሊናዊ )ከድህነት አስከፊነት ጋር ተያያዥነት ሊኖረው ይገባል ፡፡ይህም ብቻ ሳይሆን በዚህ ሁኔታ

የሳላቸው ገጸባህሪያት የሚገቡበት ትንንቅ ሁሉ ከድህነት አስከፊነት ጋር ተያያዥነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ከዚህ ፈቀቅ ያለ እንደሆነና ከጉዳዩ ጋር የማይያያዝ ሌላ የህይወት ገጽታን ቢያመጣ ያመጣው የህይወት ገጽታ ትረካ በሚወስደው ጊዜ ሳቢያ ታሪኩ በፍጥነት ከመንዝ ይገታል፡፡

ለአጭር ልቦለድ ጥድፊያ ስኬት ታዲያ አላስፈላጊ የገፀባህሪያት ገለፃ ምልልስ፣ የድርጊት ሁነቶች ዝርዝር ጉዳይ ከዋናው ታሪክ ጋር ተየያዥነት የሌለው ወይም ታሪኩን የማያሳድጉ ትርክቶች ማስወገድ ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡ ደራሲው የዋናው ገፀባህሪ አንድ ብቸኛ የሕይወት ቅንጣት የሚተርክበት የፈጠራ ስራ በመሆኑ የዋናው ገፀባህሪ ታሪክ እንኳ ቢሆን የልቦለዱ ዋና ጉዳይ ከሆነው የሕይወቱ ቅንጣት "ጥብቅ" ቁርኝት የሌለው ከሆነ ማናቸውን እውነታዎች ማምጣት የለበትም፡

ይህንን "የሚተርከው ታሪክ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ መተረክ አለበት፡ ትልሙና የተያዩ ክፍሎቹ ፍሰታቸውን ጠብቀው ዝርዝር ነገር ሳያብራሩ የተስፋፉ የመቼት ገለጻና የገፀባህሪ ጉራ ሳይሰጡ በፍጥነት መንዝ አለባቸው፡፡(ዘሪሁን፡230) በማለት ገልፆታል፡፡

አስቀድሞ እንደተጠቀሰው የመጀመሪያው አጭር ልቦለድ ዋነኛ ባህሪ ነጠላ ውጤት ለሌሎች የአጭር ልቦለድ ባህሪያት መሰረት ነው፡፡በመሆኑም ቁጥብነትን ስንፈትሽ ዋነኛው የታሪኩን አንኮር ይዘን ደራሲው እሱኑ በተቆጠበ በተመጠነ የአጭር ልቦለድ ቅርጽ በሚፈቅደው መልኩ እንዴት አቀረበው የሚለውን እንፈትሻለን፡፡

አጭር ልቦለድ በባህሪው ጥድፊያ ይታይበታል፡፡ ጥድፊያ የአጭር ልቦለድ የታሪክ ጉዞ ፈጣንነት የሚመለከት ነው፡፡ በአጭር ልቦለድ አዝግሞ የሚሄድ ታሪክ የለም፡፡ ከአጀማመሩ ለምሳሌ የገጸባህሪ እውቂያ፣ የመቼት ገለጻ፣ ወዘተ ከተሰጠበት እስከ ታሪኩ ፍጻሜ ድረስ የሚከናወኑ ድርጊቶች ሁሉ በአጭር ልቦለድ የሚንቀሳቀሱት ጥድፊያ ባልተለየው በፍጥነት ነው፡፡ በመሆኑም ጥድፊያ በአጭር ልቦለድ ውስጥ የሚታይ የስነጽሑፍ ዘሩ ባህሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ጥድፊያ በአጭር ልቦለድ ሁለንተናዊነት ላይ ይታያል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ጥድፊያ በአጭር ልቦለድ ውሰጥ በአላባዊያን ረገድ ብዙ ጊዜ በተጨባጭ ይገለጻል፡፡ ለምሳሌ በአጭር ልቦለድ ጥድፊያን በግጭት አላባ አንጻር መመልከት ይቻላል፡፡ በመሰረቱ  በአንድ አጭር ልቦለድ

ውስጥ ዕውቂያ እንደተፈጸመ ወዲያው በበቂ ምክንያት ግጭቱ ይፈጠራል፤ ያድጋል፤ ዕድገቱም እየተወሳሰበ ሄዶ እጡዘት ይደርሳል፤ከዚያም ወዲያው

ችግሩ እየተፈታ ሄዶ ልቀት ላይ ይደርሳል - መፍትሔ ያገኛል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚያልፍ ግጭት አንድ አጭር ልቦለድ ካለው ያ አጭር ልቦለድ ጥድፊያ አለው ሊባል ይቻላል፡፡ እነደዚሁ በሌሎች የልቦለድ አላባዊያንና  ልቦለድ ግልጋሎት ላይ የሚውሉ ጥድፊያን በተላበሰ ሁኔታ ሲሆን አንድ አጭር ልቦለድ የጥድፊያ ባህሪውን እንዳሟላ ይገመታል ፡፡

በሌላ በኩል በአጭር ልቦለድ የታሪኩን ፈጣን ጉዞ የሚገቱ ጉዳዮችን / ነገሮችን በመግታት ለአንድ አጭር ልቦለድ ጥድፊያን ማቀዳጀት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አንድ የአካባቢ ገለጻ ለአጭር ልቦለዱ ታሪክ የማያስፈልግ ከሆነ መቅረት አለበት፡፡ ፍጥነትን ለአጭር ልቦለድ የሚያቀዳጁት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ብቻ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ተካተው ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ማንኛውም ነገር ይሁን በአጭር ልቦለድ ውስጥ የማይፈለግ ከሆነ እጥቅም ላይ መዋል የለበትም፡፡ አለአስፈላጊ ገለጻ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ቦታ የላቸውምና፡፡በመሆኑም አጭር ልቦለድ ፍጥነት ይኖረው ዘንድ የማያስፈልጉ የታሪክ ገጽታዎችን ደራሲው እየጠቀለለ ወይም እየዘለለ በዋናው ታሪክ ላይ ብቻ በማትኮር መጓዝ ይኖርበታል፡፡ የተተዉ ወይም የተጠቀለሉ ታሪኮች በአጭር ልቦለድ ውስጥ ለአንባቢው የሚተዉም ናቸው፡፡

ውድ ተማሪዬ! አጭር ልቦለድ ፍጥነት ያለው ስነጽሁፍ ነው ሲባል የሚተረከው ታሪክ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ መተረክ አለበት፡፡ ትልሙና የተለያዩ ክፍሎች ዝርዝር ነገር ሳያበዙ … በፍጥነት መጓዝ አለባቸው ሲሉ ዘሪሁን፣ /1992፣230/ ይገልጻሉ፡፡

አጭር ልቦለድ አለአስፈላጊ የታሪኩን አካል እየዘለለ ወይም እየጠቀለለ ወደ ዋናው ታሪክ መጓዙ በርግጥ ፍጥነትን ለልቦለዱ ያቀዳጃል፡፡ አጭር ልቦለድ ታሪክ ካንድ ድርጊት ወደ ሌላው ድርጊት የሚያደርገው ጉዞ ፈጣን ነው፡፡ እንደ ረጅም ልቦለድ ታሪክ አጭር ልቦለድ ዘና እያለ እየተጠማዘዘ አይጓዝም፡፡ ዘርፍ ታሪክም አያበጅም፡፡ ከህይወት ውስጥ በአንዲት ቅንጣት ገጠመኝ ላይ አጭር ልቦለድ ማትኮሩም ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለው ጉዞ ፈጣን እንዲሆን  አስችሎታል፡፡